5-01760/09
09 ሰኔ 2009

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ethiopian Revenues and Customs Authority

በአባሪው ለተዘረዘሩት በሙሉ

ጉዳዩ፡- የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች የሥጋት ሥራ አመራር የአሰራር ማኑዋልን ይመለከታል

ባለሥልጣን መ/ቤታችን የአገልግሎት አሰጣጡን የተቀላጠፈና ግልጽ እንዲሆን ለማስቻል የተለያዩ እርምጃዎችን እየወሰደ እንደሚገኝ ይታወቃል፡፡ ከነዚህም አንዱ የአሰራር ማኑዋሎችን በማዘጋጀት ስራዎች ግልጽ እና በሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች የሚደረጉ ተመሳሳይ አሰራሮች ወጥነትና ተጠያቂነት እንዲኖራቸው ማስቻል ነው፡፡

ይህንን ታሳቢ በማድረግ ቀደም ሲል የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች የሥጋት ሥራ አመራር የአሰራር ማኑዋል ተዘጋጅቶ በደብዳቤ ቁጥር 3.0/273/07 ሐምሌ 29/2007 ዓ.ም በስጋት ሥራ አመራር ኮሚቴ በማፀደቅ ወደ ስራ መግባቱ ይታወሳል፡፡ ሆኖም ግን አሁን ካለው ነባራዊ ሁኔታ በመነሳት ማኑዋሉን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ማሻሻያዎችን በማድረግ በሥጋት ሥራ አመራር ኮሚቴው እንዲጸድቅ ተደርጓል፡፡ በዚሁ መሰረት ይህ ደብዳቤ ወጪ ከሆነበት ቀን ጀምሮ በሁሉም የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች ማኑዋሉ ተግባራዊ እንዲደረግና የሥጋት ሥራ አመራር ሥርአቱ ማኑዋሉን መሰረት አድርጎ በወጥነት ተግባራዊ እንዲደረግ እያሳሰብኩ የማኑዋሉን ቅጅ 49 ገጽ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ ተደርጎ መላኩን አስታውቃለሁ፡፡

ከሠላምታ ጋር

ዘመዴ ተፈራ
የህግ ማስከበር ሥራዎች ዘርፍ
ምክትል ዋና ዳይሬክተር

ግልባጭ፣

- ለክቡር ዋና ዳይሬክተር
- ለጉምሩክ ፕሮግራም ልማትና ድጋፍ ሥራዎች ዘርፍ
- ለሞደርናይዜሽንና ኮርፖሬት ሥራዎች ዘርፍ
- ለአገር ውስጥ ፕ/ል/ሥ/ዘርፍ
- ለአዲስ አባባ አገር ውስጥ ታክስ አሰራር ፕ/ል/ሥ/ዘርፍ
- ለጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ፕሮግራም ልማትና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
- ለመረጃ ቴክኖሎጂ ሥራ አመራር ዳይሬክቶሬት
- ለድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ፕሮግራም ልማትና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
- ለታክስ ህግ ተገዥነት ሥጋት ሥራ አመራር ዳይሬክቶሬት
- ለዋጋና ታሪፍ ምደባ አሰራርና ፕሮግራም ልማት ዳይሬክቶሬት
- ለኢንተለጀንስ ዳይሬክቶሬት
- ለደንበኞች አገልግሎት ዳይሬክቶሬት
- የግብር አወሳሰንና አሰባሰብ እ/ፕ/ል/ዳይሬክቶሬት
  ኢ/ገ/ጉ/ባ
- ለከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
  አዲስ አባባ

- ለአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
- ለአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

  <u>አዲስ አበባ</u>
- ለአዳማ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

  <u>አዳማ</u>
- ለሞጆ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

  <u>ሞጆ</u>
- ለድሬዳዋ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

  <u>ድሬዳዋ</u>
- ለኮምቦልቻ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

  <u>ኮምቦልቻ</u>
- ለመቀሌ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

  <u>መቀሌ</u>
- ለሚሌ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

  <u>ሚሌ</u>
- ለጋላፊ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

  <u>ጋላፊ</u>
- ለባሕር ዳር ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

  <u>ባህር ዳር</u>
- ለጅጅጋ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

  <u>ጅጅጋ</u>
- ለሞያሌ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

  <u>ሞያሌ</u>
- ለሀዋሳ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

  <u>ሀዋሳ</u>
- ለጅማ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

  <u>ጅማ</u>
- ለከፍተኛ ግብር ከፋዮች

  [illegible]

# የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን

## የታክስ ህግ ተገዥነት ስጋት ሥራ አመራር ዳይሬክቶሬት

## የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች ስጋት ሥራ አመራር የአሠራር ማኑዋል

ሁለተኛ ዕትም

ሰኔ 2009 ዓ.ም

አዲስ አበባ

## ማውጫ


ምዕራፍ አንድ ........ 2

1.1. መግቢያ ........ 2

1.2. የተቋሙ/የዳይሬክቶሬቱ ራዕይና ተልእኮ መግለጫ ........ 4

1.3. ዓላማ ........ 5

1.4. አስፈላጊነት ........ 5

1.5. የተፈጻሚነት ወሰን ........ 6

ምዕራፍ ሁለት ........ 9

የስጋት ስራ አመራር የአሰራር ፍሰት ........ 9

2.1. የተግባራት ቅደም ተከተል (ደረጃዎች) ........ 9

2.1.1. የመጀመሪያ ደረጃ፡- የስጋት ማዕቀፍ ማስቀመጥ ........ 11

2.1.2. ሁለተኛ ደረጃ፡- ስጋቶችን መለየት፤ ........ 11

2.1.3. ሶስተኛ ደረጃ፡- መረጃ ማሰባሰብ እና ማደራጀት፤ ........ 12

2.1.4. አራተኛ ደረጃ፡- ስጋትን መተንተን እና የስጋት ደረጃ ማውጣት፤ ........ 13

2.1.5. አምስተኛ ደረጃ፡- ሥጋትን መመዘን እና ማስተናገድ፤ ........ 16

ምዕራፍ ሦስት ........ 17

የገቢ ዕቃ አወጣጥ ሥጋት አጣጣል ........ 17

3.1. ስድስተኛ ደረጃ፡ ስጋትን መጣልና በሲስተም የተጣለ ስጋትን ማሻሻል፤ ........ 17

3.1.1. በሲስተም ስጋት መጣል በማይቻልበት ሁኔታ ሥጋትን መጣል፡ ........ 17

3.1.2. በሲስተም የተጣለን የስጋት ደረጃ በማኑዋል ማሻሻል (manuall Intervention) ፤ ........ 23

ምዕራፍ አራት ........ 36

የገቢና ወጪ ዕቃዎች ትራንዚት ቁጥጥር (የካርጎ ስካኒንግ ፍተሻ) ስጋት ደረጃ አጣጣል፤ ........ 36

4.1. የገቢ ዕቃዎች ትራንዚት ቁጥጥር (የካርጎ ስካኒንግ ፍተሻ) ስጋት ደረጃ አጣጣል፤ ........ 36

4.2. የወጪ ትራንዚት ቁጥጥር (የካርጎ ስካኖንግ ፍተሻ) ስጋት ደረጃ አጣጣል፤ ........ 39

የተግባር መግለጫ ........ 39

ምዕራፍ አምስት ........ 41

የገቢ መንገደኞች የስጋት ደረጃ አጣጣል፤ ........ 41

ምዕራፍ ስድስት ........ 44

የወጪ ዕቃዎች ስጋት አመዳደብ ........ 44

ምዕራፍ ሰባት ........ 47

ደረጃ አምስት፡ የስጋት ደረጃዎችን ውጤት መከታተል እና መገምገም ........ 47

# ምዕራፍ አንድ

## 1.1. መግቢያ

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ዘመናዊ የጉምሩክ አስተዳደርን ለመገንባት ዘርፈ ብዙ ጥረቶችን እያደረገ ይገኛል። ከዚህም አንዱና ዋነኛው የጉምሩክ አሠራርን ሙሉ በሙሉ የስጋት ሥራ አመራርን መሠረት ያደረገ ሆኖ የተቀላጠፈ አገልግሎትና ቁጥጥር የተጣጣመ እንዲሆን ማስቻል ነው። የሥጋት ሥራ አመራር ዓለም አቀፋዊ ይዘት ያለው የአሠራር ሥርዓት ሲሆን ለህጋዊ ነጋዴዎች የተቀላጠፈ አገልግሎት መስጠት፣ ለህጉ ተገዥ ባልሆኑት ላይ ደግሞ ተገቢውን ቁጥጥር ለማድረግ እና ወደ ህግ ተገዥነት ለማምጣት የሚያስችል ዘመናዊ የአሰራር ዘዴ ነው። መረጃዎችን ከተለያዩ ምንጮች በመሰብሰብና ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ በመተንተን ፈጣን አገልግሎት አሰጣጥን ከውጤታማ ቁጥጥር ጋር አጣጥሞ ለመተግበር የሚያስችል ስልት ነው።

ከዚህ ጋር በተያያዘ ባለሥልጣኑ ገቢን በብቃት ለመሰብሰብ፣ ኮንትሮባንድን ለመከላከል እና የህብረተሰቡን ደህንነት ለመጠበቅ በገቢና ወጪ ዕቃዎች ላይ የሚደረገውን ቁጥጥር ስጋትን መሠረት ባደረገ አኳኋን እንዲፈፀም እየሰራ ይገኛል። እነዚህ ሥራዎች በተገቢው ሁኔታ ማከናወን ይቻል ዘንድ ወጥነት ያለው የሥጋት ሥራ አመራር ማኑዋል መቅረጽና ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ ነው። በሥጋት ሥራ አመራር ያልተደገፈ አገልግሎት አሰጣጥ ንግድን የማሳለጥ ተግባር ከማስተጓጎሉ ባለፈ ቁጥጥር ሊደረግባቸው የሚገቡ ስጋቶችን ለይቶ ትኩረት ማድረግ ሲገባው በሁሉም ላይ ቁጥጥር በማድረግ አላስፈላጊ የሆነ መስተጓጎል እንዲሁም የሃብት ብክነት ያስከትላል።

የጉምሩክ ቁጥጥርን የስጋት ሥራ አመራርን መሰረት ባደረገ መልኩ ተግባራዊ ማድረግ ዘርፈ ብዙ ጥቅሞች ሲኖሩት በዋናነት ንግድና ኢንቨስትመንትን ለመደገፍ፣ ህጋዊ ነጋዴዎችን ለማበረታት እና ህገ-ወጥ የንግድ እንቅስቃሴዎችን ለመቆጣጠርና ወደ ህጋዊ ሥርዓት ለማምጣት ከፍተኛ ሚና አለው። ስለሆነም ይህ የአሰራር ማኑዋል ከዚህ በፊት የነበረውን ማኑዋል መነሻ በማደረግ ግልጽነትና ተጠያቂነት በሚያሰፍን መልኩ ሥራዎችን ለማከናወን ያለመ ነው።

ማኑዋሉ ሲዘጋጅ በሀገሪቱ የሚገኙ ሁሉም የጉምሩክ ኬላዎችና መቅረጫ ጣቢያዎች ላይ የሚደረጉ የቁጥጥር ሥራዎች በአውቶሜሽን ሲስተም የታገዘ እንደሚሆን ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው። በመሆኑም አሁን ያለው የሲስተም የጥራት ክፍተትና መቆራረጥ ተቋሙ በሚሰራቸው የተለያዩ ሥራዎች እና የሥጋት ሥራ አመራር ዳይሬክቶሬት የተቋሙን ስጋት ሥራ አመራር በተሻለ መልኩ ለማዘመን በሚያከናውናቸው ተግባራት የተሻሉ እንደሚሆን ይታመናል። ይህንንም እውን ለማድረግ በየቅ/ጽ/ቤቶች የስጋት ስራ አመራር ስራዎችን በማጠናከር ኦፕሬሽናል የሆኑ ስጋቶችን ለመቆጣጠር እና ወቅታዊ የሆኑ ተለዋዋጭ ሁኔታዎችን ታሳቢ በማድረግ አገልግሎቱን ማፋጠን ያስፈልጋል። በመሆኑም ሲስተም የጣለውን የስጋት ደረጃ በባለሙያዎች ጣልቃገብነት ማሻሻያ ማድረግ ሲያስፈልግ፤ በአውቶሜሽን ሲስተም የስጋት ደረጃ መጣል ሳይቻል ሲቀር ባለሙያዎች ስጋት እንዲጥሉ፤ ሲስተም በጣለው ስጋት ጣልቃ ገብተው እንዲያሻሽሉ የሚጋብዙ ሁኔታዎችና መነሻ ሃሳቦች በዚህ ማኑዋል ተካተዋል።



... Revenues and Customs ... Archive & Documentation ...

## 1.2. የተቋሙ/የዳይሬክቶሬቱ ራዕይና ተልእኮ መግለጫ

ከተቋሙ የተመነዘረ የዳይሬክቶሬቱ ራእይ እና ተልእኮ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

| | የተቋሙ | የዳይሬክቶሬቱ |
|---|---|---|
| ራዕይ | በ2017 በአፍሪካ ግንባር ቀደም የሆነ ዘመናዊና ፍትሐዊ የታክስ አስተዳደር ሰፍኖ አገራዊ ወጪ በአገራዊ ገቢ ተሸፍኖ ማየት፤ | ተቋሙ የዘመነ፤ ፈጣን፤ ፍትሓዊ እና ግልፀኝነት ያለው በአፍሪካ ግንባር ቀደም የታክስ ህግ ተገዥነት ስጋት ስራ አመራር ስርዓት አፈፃፀም ያለው ሆኖ ማየት፤ |
| ተልዕኮ | ታክስና ቀረጥን በፈቃደኝነት የመክፈል ባህልን በማዳበር ህግን ሊያስከብር የሚችል ሙያዊ ብቃትና ተነሳሽነት ያለው ባለሙያ በመጠቀም፣ ዘመናዊ የታክስ እና ቀረጥ አስተዳደር ስርዓት በመዘርጋት፣ ለሃገር ልማት የሚውል ገቢ በብቃት በመሰብሰብ የዜጐችን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ደህንነት ማረጋገጥ | ዘመናዊ፤ ግልጽነትና ተጠያቅነት ያለው የታክስ ህግ ተገዥነት ስጋት ስራ አመራር ሥርዓት በመዘርጋት ተገልጋዮች ፈጣንና ቀልጣፋ አገልግሎት እንዲያገኙ በማድረግ እና የተ የተቋሙን የግብርና ቀረጥ አሰባሰብ ሥርዓቱን ማገዝ፤ |
| እሴቶች | ደንበኛ ተኮር አገልግሎት መስጠት፤ የሕብረተሰቡን ደህንነት መጠበቅ፤ ከብልሹ ምግባር የፀዳ የሥራ አካባቢ፣ ሙያዊ ክህሎትን ለተጨባጭ ውጤት መጠቀም (Professionalism) ህግን ማስከበር፤ በቡድን መስራት፤ የሴቶችን ተሳትፎ ማረጋገጥ፤ | ዳይሬክቶሬቱ የተቋሙን እሴቶች ይተገብራል፤ |
| አላማዎች | ዘመናዊ የገቢ አወሳሰንና አሰባሰብ ሥርዓት በመዘርጋት ለተገልጋዮች ፍትሐዊ፣ ቀልጣፋና ጥራት ያለው አገልግሎት መስጠት፣ ታክስ ከፋዩ ግዴታውን በፍቃደኝነት እንዲወጣ ማስቻል፣ ኮንትሮባንድ፤ የታክስ ማጭበርበርና ስወራን | • የጉምሩክ የቁጥጥር እና የተሳለጠ አገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓት አፈፃፀም የተጣጣመ ማድረግ፤<br>• ፈጣን ፍትሀዊ እና ቀልጣፋ የታክስ ህ ተገዥነት ስጋት ስራ አመራር አገልግሎት ለመስጠት የጉምሩክና የታክስ ስነ ስርዓ |

| | | |
|---|---|---|
| | በመከላከልና በመቆጣጠር የታክስና የጉምሩክ ሕግጋትን ማስከበር፣ ኢኮኖሚው የሚያመነጨውን የታክስ ገቢ በብቃትና በወቅቱ መሰብሰብ፣ የፌዴራልና የክልል ታክስ አስተዳደር ሥርዓቶች የተጣጣሙ እንዲሆኑ ለማድረግ ለክልሎች አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ፤ | በመረጃ ቴክኖሎጂ እንዲደገፍ ማድረግ እና<br>• ለልማታዊ ባለ ሀብቶች ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር፤ ልዩ የጉምሩክ አገልግሎት ተጠቃሚዎች እና የተመረጡ የኢኮኖሚ እንቀሳቀሽ (AEO) ስርዓትን ማስፋፋት እና ማጠናከር፣<br>• በጉምሩክ እና በታክስ አሠራር ላይ የሚታዩ ክፍተቶችንና ስጋቶች መለየት እና ማስተናገድ፣ አዳዲስ ስጋቶች የሚስተናገዱበት ሥርዓቶችን መቅረፅ፣ |

## 1.3. ዓላማ

የዚህ ማንዋል ዓላማ በሁሉም የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች ከሥጋት ስራ አመራር ጋር በተያያዘ የሚሰሩ ሥራዎችን በመለየትና እንዴት እንደሚሰሩ እንዲሁም ተጠያቂነትንና ኃላፊነትን በግልፅ በማስቀመጥ በየደረጃው ለሚገኙ ፈፃሚዎችና የሥራ ኃላፊዎች የስጋት ደረጃን በተመለከተ የሚወሰኑት ውሳኔዎች ወጥነት እና ግልጽነት ባለው መልኩ እንዲፈፀሙ ማስቻል ነው፡፡ በተለይ አውቶሜሽን ሲስተም የጣለው የስጋት ደረጃዎች ላይ ማሻሻያ ማደረግ ሲያስፈልግ በማኑዋል ለማሻሻል እና አውቶሜሽን ሲስተም በተለያዩ ምክንያቶች የስጋት ደረጃ በማይጥልበት ጊዜ የስጋት ስራ አመራር ባለሙያዎች በጊዜያዊት ሲስተሙን ተክተው በማኑዋል የስጋት ደረጃዎችን ለመጣል የሚያስችል ዝርዝር አሰራር ለማስቀመጥ ያለመ ነው፡፡ በተጨማሪም ይህ ማኑዋል የሥጋት ሥራ አመራር የሥልጠና ስነድ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል፡፡

## 1.4. አስፈላጊነት

የዚህ ማኑዋል አስፈላጊነት የስጋት ስራ አመራር መርህ በአዋጅ 859/2008 እና በሥጋት ሥራ አመራር ፖሊሲው በጥቅል የተገለጸ በመሆኑ፤ ሥጋት በባህሪው ተለዋዋጭ በመሆኑ እና አሠራሩን በመመሪያ ለማስቀመጥ ስለማይቻል ፈጻሚዎች ሥራዎቻቸውን በቀላሉ በግልጽነትና ተጠያቂነት ለማከናወን የሚረዳ የአሰራር ማኑዋል ለማስቀመጥ ነው፡፡

## 1.5. የተፈጻሚነት ወሰን

ማኑዋሉ በማንኛውም የትራንዚት፣ የገቢ ዕቃዎች፣ የወጪ ዕቃዎች፣ ገቢ መንገደኞች እና የጉምሩክ ስነ-ስርዓት የሚፈጸምባቸው መቅረጫ ጣቢያዎች የሚፈጸም ሲሆን ለሀገር ውስጥ ታክስ ተፈጻሚ አይሆንም።

## 1.6. ትርጉም

1) "ስጋት" ማለት የአንድ ተቋም ዓላማዎች እንዳይሳኩ የሚያደርጉ ውስጣዊና ውጫዊ አሉታዊ ክስተት(ቶች) ሲሆን ከጉምሩክ አንጻር ስጋቶች ዋጋ ማሳነስና ማብዛት፣ የታሪፍ ቁጥር ማሳሳት፣ የስሪት ሀገር ማሳሳት፣ የዕቃ መግለጫ ማሳሳት፣ በሰነድ ከተገለፀው ብዛት እና አይነት የተለየ ዕቃን ማምጣት፣ ኮንትሮባንድ፣ የቀረጥ ነጻና የመጋዘን እንዲሁም ሌሎች ልዩ መብቶችን አለአግባብ መጠቀም፣ ቀልጣፋ አገልግሎት አለመስጠት፣ የተቋሙን ዓላማ መሳካት የሚጎዱ የሥነ-ምግባር ግድፈት የመሳሰሉት ናቸው።
2) "የስጋት ስራ አመራር" ማለት ስጋቶች ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ የሚለዩበት፣ የሚተነተኑበት፣ የሚስተናገዱበት እና የሚገመገሙበት የሥራ አመራር ጥበብ ሲሆን በዚህም ዕድሎች የሚለዩበት እና ሊፈጠር የሚችልን ኪሳራ እንዲቀንስ የሚደረግበት የአሰራር ዘዴ ነው። በተመሳሳይ በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 2 ቁጥር 45 መሰረት የስጋት ስራ አመራር ማለት ወደ ጉምሩክ ክልል በሚገቡ፣ በሚወጡና በሚተላለፉ ዕቃዎች ላይ አገልግሎት አሰጣጡንና የቁጥጥር ሥርዓቱን ሚዛናዊ ባደረገ ሁኔታ በሚቀመጡ መስፈርቶች መሠረት የተለያየ የስጋት ደረጃ በማውጣት የሚከናወን የአሰራር ሥርዓት ነው።
3) "የጉምሩክ ትራንዚት" ማለት ዕቃዎች ወይም መንገደኞች በጉምሩክ ቁጥጥር ስር ሆነው ከአንድ የጉምሩክ ጣቢያ ወደ ሌላ የጉምሩክ ጣቢያ የሚተላለፉበት የጉምሩክ ስነ ሥርዓት ነው።
4) "ተላላፊ መንገደኛ" ማለት የትራንዚት አካባቢውን እስካለቀቀ ድረስ በጉምሩክ ቁጥጥር አይደረግበትም። ሆኖም ባለሥልጣኑ በትራንዚት አካባቢው ላይ የጉምሩክ ወንጀል ተፈጽሟል የሚል ጥርጣሬ ሲኖረው አስፈላጊውን ማጣራት እና እርምጃ መውሰድ የችላል።

5) "መንገደኛ"፡ ማለት መደበኛ መኖሪያው በኢትዮጵያ ውስጥ ያልሆነ እና ወደ ሀገር የሚገባ ወይም ከአገር የሚወጣ ወይም መደበኛ መኖሪያው በኢትዮጵያ ውስጥ ሆኖ ከአገር የሚወጣ ወይም ወደ አገር የሚመለስ ሰው ነው።

6) "ካርጎ ስካኒንግ ማሽን" ማለት ወደ ሀገር የሚገቡ ወይም ከሀገር የሚወጡ ተሽከርካሪዎች የያዟቸው ጭነቶች ወይም ከአገር የሚወጡ እና ወደ ሀገር የሚገቡ ጓዞች የሚፈተሹበት የዕቃ መፈተሻ መሳሪያ ነው።

7) "ቀይ ስጋት ደረጃ" ማለት ከፍተኛ የስጋት ደረጃ ማለት ሲሆን በፍተሻ መመሪያ መሰረት አካላዊ የዕቃዎች ወይም የመንገደኞች ፍተሻ እና የሠነድ ምርመራ እንዲደረግ የሚገልጽ መስመር (channel) ነው።

8) "ቢጫ ስጋት ደረጃ" ማለት መካከለኛ የስጋት ደረጃ ማለት ሲሆን ሰነድ ምርመራ እንዲደረግ የሚገልጽ መስመር (channel) ነው።

9) "አረንጓዴ ስጋት ደረጃ" ማለት ዝቅተኛ የስጋት ደረጃ ማለት ሲሆን በመድረሻ ጣቢያ የደረሱ ዕቃዎች ወይም መንገደኞች የሰነድና የአካላዊ ፍተሻ ሳይደረግባቸው የገቢ ዕቃ ሰነድ እንደቀረበ ወይም መንገደኛው እንደደረሰ በመልቀቅ በድህረ- ዕቃ አወጣጥ ኦዲት እና በሌሎች ዕቃ ከተለቀቀ በኋላ ቁጥጥር በሚያደርጉ የህግ ማስከበር የስራ ክፍሎች ቁጥጥር ሊደረግባቸው የሚችሉ መሆኑን የሚገልጽ መስመር ነው።

10)"ሰማያዊ ስጋት ደረጃ" ማለት በዝቅተኛ የስጋት ደረጃ የሚመደቡ የተመረጡ የኢኮኖሚ እንቀሳቃሽ ድርጅቶች(AEO) የሚስተናገዱበት የስጋት ደረጃ ሲሆን፤ በመድረሻ ጣቢያ የደረሱ ዕቃዎች የሰነድና የአካላዊ ፍተሻ ሳይደረግባቸው የገቢ ዕቃ ሠነድ እንደቀረበ ተለቀው በድህረ- ዕቃ አወጣጥ ኦዲት እና በሌሎች የህግ ማስከበር የስራ ክፍሎች ዕቃው ከተለቀቀ በኋላ ቁጥጥር ሊደረግባቸው የሚችሉ መሆኑን የሚገልጽ መስመር ነው።

11)"ብርቱካናማ የስጋት ደረጃ" ማለት ወደ ሀገር ውስጥ ሊገቡ ወይም ሊወጡ የተዘጋጁ ዕቃዎችን የጫኑ ተሽከርካሪዎች በከፍተኛ የሥጋት ደረጃ ላይ መሆናቸውን የሚገልጽ መስመር (channel) ሲሆን በስካኒንግ ማሽን ወይም አካላዊ ፍተሻ እንዲደረግባቸው የሚገልጽ መስመር ነው።

12)"ነጭ ስጋት ደረጃ" ማለት ወደ ሀገር ውስጥ ሊገቡ ወይም ሊወጡ የተዘጋጁ ዕቃዎችን የጫኑ ተሽከርካሪዎች በዝቅተኛ የስጋት ደረጃ ላይ መሆናቸውን የሚገልጽ መስመር

(channel) ሲሆን፤ በስካኒንግ ማሽን ወይም አካላዊ ፍተሻ ሳይደረግባቸው እንዲለቀቁ የሚገልጽ መስመር ነው፡፡

13)**"የልዩ መብት ተጠቃሚ"** ማለት በተቋሙ በተቀመጠ የአሰራር ሥርአት መሰረት ተመርጠው የተቀላጠፈ መስተንግዶ እንዲያገኙ የሚደረጉ ድርጅቶች ናቸው፡፡

14)**"የተመረጡ የኢኮኖሚ እንቀሳቃሾች "** ማለት በአቅርቦት ሰንሰለት ተሳታፊ የሆኑና በባለሥልጣኑ የተዘጋጁ ዝቅተኛ መስፈርቶችን በማሟላት በተመረጡ የኢኮኖሚ እንቀሳቃሽ ፕሮግራም የታቀፉ ሰዎች/ድርጅቶች ማለት ነው፡፡

15)**"የስጋት ስራ አመራር ደረጃ"** ማለት በተደረገ የስጋት ትንታኔ መነሻ ወይም በተቀመጠ የስጋት መስፈርት መሰረት የአንድን ዕቃ፣ ተሽከርካሪ ወይም መንገደኛ የመስተንግዶ መስመር የሚገልጽ ነው፡፡

16)**"የጉምሩክ ዋጋ ዝርዝር መግለጫ** (Valuation Details Declaration [VDD])" ፡- ማለት ከዕቃ ዲክሌራሲዮን በተጨማሪ የገቢ ዕቃዎችን የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ ለመተመን የሚያስፈልጉ መግለጫዎችና መረጃዎችን በዲክላራሲዮን አቅራቢው በመሙላት ለባለስልጣኑ በዝርዝር የሚያሳውቅበት በባለሥልጣኑ የተዘረጋ ሥርዓት ወይም የተዘጋጀ የኤሌክትሮኒክ መረጃ ማሳወቂያ ሥነ-ሥርዓት ሲሆን፤ በወረቀት መልክ የሚዘጋጅ ቅጽንም ይጨምራል፡፡

17) **"የኢትዮጵያ የጉምሩክ ዋጋ መረጃ ሥርዓት** (Ethiopian customs valuation system [ECVS]) "፡- ማለት በባለሥልጣኑ ተቀባይነት ያገኙ የገቢ ወይም ወጪ እቃዎች ዋጋ መረጃን እና የአለማቀፍ ዕቃዎች ዋጋ መረጃን መሠረት በማድረግ የሚደራጅ ለዋጋ ማነጻጸሪያነት የሚያገለግል የመረጃ ዳታቤዝ ነው፡፡

18) "Tax Payear Risk Data Profile (TPRDP)"፡- የግብር ከፋዮች ከጥፋት ጋር በተያያዘ መረጃ የሚደራጅበት ዳታ ቤዝ ነው

19)"ባትሎአድ" ፡- ማለት ባህር ትራንዚት ሎጅስቲክ አገልግሎት ድርጅት

20) **"ቅ/ጽ/ቤት"**፡-ማለት የጉምሩክ ስነስርአት የሚፈጸምባቸው የባለስልጣኑ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ናቸው፡፡

21) **"አዋጅ"** ማለት የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 ነው፡፡

22) "ፖሊሲ" ማለት የኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለስልጣን የስጋት ስራ አመራር ፖሊሲ ነው፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# የስጋት ስራ አመራር የአሰራር ፍሰት

## 2.1. የተግባራት ቅደም ተከተል (ደረጃዎች)

1ኛ. ማዕቀፍ ማስቀመጥ

2ኛ. ስጋቶችን መለየት


3ኛ. መረጃ ማሰባሰብና ማደራጀት

4ኛ. ስጋትን መተንተንና የስጋት ደረጃ ማውጣት

5ኛ. ሥጋትን መመዘን እና የመስተንግዶ ስትራቴጂ መቅረጽ።

6ኛ. የስጋት ደረጃዎች ውጤት መከታተል እና መገምገም።

የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች ስጋት ስራ አመራር ስርዓት ስጋትን የመተንተን የአሰራር ሂደት ፍሰት ስእላዊ መግለጫ



### 2.1.1. የመጀመሪያ ደረጃ፡- የስጋት ማዕቀፍ ማስቀመጥ

የስጋት ማዕቀፍ ማስቀመጥ ማለት የተቋሙን ወይም የቅ/ጽ/ቤቱን ስጋት ለማስተዳደር ከግምት ውስጥ ሊያስገባቸው የሚገቡ አጠቃላይ ውጫዊና ውስጣዊ ሁኔታዎች ናቸው። እነዚህም አጠቃላይ የኢኮኖሚ፣ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ሁኔታዎችን የሚዳስሳ ሲሆን በተጨማሪም የውስጥ ተቋማዊ እንዲሁም የቅ/ጽ/ቤቱን አደረጃጀት እና ብቃት፣ ቴክኖሎጂ ለጉምሩክ አሰራር ስርዓት የሚኖረውን አወንታዊ እና አሉታዊ ተጽዕኖ የሚተነተንበት ሂደት ነው።

### 2.1.2. ሁለተኛ ደረጃ፡- ስጋቶችን መለየት፤

**የተግባር መግለጫ**

በየወቅቱ ሊከሰቱ የሚችሉ እና የተከሰቱ ስጋቶችን በቀጣይነት መለየት፤

**አስፈላጊነት/Purpose**

ስጋቶች የሚለዩት ስጋቶች እንዳይከሰቱ ወይም ከተከሰቱም በኋላ ከፍተኛ ችግር ሳያስከትሉ ስጋት የመ/ቤቱ ለመቆጣጠር የሚያስችል አሰራር ለመንደፍና የስጋት ትንተና ለማከናወን ነው። ስጋት የመ/ቤቱ ዓላማዎች ወይም ግቦች እንዳይሳኩ የሚያደርግ ማንኛውም አሉታዊ ተጽኖ ሲሆን አሁን ባለው የጉምሩክ አሰራር ዋና ዋናዎቹ የጉምሩክ ስጋቶች የሚባሉት ህገ-ወጥ ንግድ (ኮንትሮባንድ)፤ ንግድ ማጭበርበር፤ የዕቃዎች የስሪት ሀገር ማሳሳት፣ በመንግስት የተሰጡ መብቶች አለአግባብ መጠቀም፤ የተከለከሉና ገደብ የተደረገባቸው ዕቃዎች ማስገባት ወይም ማስወጣት ሲሆን በአጠቃላይ በጉምሩክ አዋጅ 859/2006 መሰረት የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ሳይከናወን ሲቀር ስጋት ተከስቷል ሊባል ይችላል።

**የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎች**

ከተለያዩ የሥራ አካላት ጋር ግንኙነት መፍጠር

- የውስጥ ባለድርሻ አካላት
  - ገቢና ወጪ ዕቃ አወጣጥ ጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አፈጻጸም፤
  - የገቢ ዕቃ እና የወጪ ዕቃ ትራንዚት
  - መጋዘን አስተዳደር
  - ህግ ማስከበር
  - ድህረ-ዕቃ አወጣጥ

- ሌሎች የሥራ ክፍሎች (ደንበኞች አገልግሎት፣ ድንገተኛ ፍተሻ፣ ኢንተለጀንስ፣ ህግ ፣ፓትሮሊንግ እና ኮንትሮባንድ ክትትል)

➢ የውጭ ባለድርሻ አካላት

✓ ምርመራ እና ዐቃቤ ህግ

✓ በየቅ/ጽ/ቤቱ ያሉ ተቆጣጣሪ መ/ቤቶች፣ የጉምሩክ አስተላላፊዎች እና ፈቃድ ሰጪ መ/ቤቶች እና ከተቋሙ ጋር ግንኙነት ያላቸው አካላት ናቸው።

✓ ጥንካሬ እና ድክመቶችን መለየት

➢ በጉምሩክ አሰራር፣ አዋጆች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች፣ ማኑዋሎች፣ ሰርኩላሮች እንዲሁም ጉምሩክ የሚያስፈጽማቸው ሌሎች ህጎችን የተለያዩ ጥናቶችን በማካሄድ በመገምገም እና በመፈተሽ

**የአፈፃፀም ቅደም ተከተል/ Procedures**

➢ ያጋጠሙ ስጋቶችን መለየት (የውስጥ እና የውጪ ሥጋቶች)፣

➢ የተለዩ ስጋቶችን ትክክለኛነታቸውን ማጣራት፤

## 2.1.3. ሶስተኛ ደረጃ፡- መረጃ ማሰባሰብ እና ማደራጀት፤

**የተግባር መግለጫ**

ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች ለስጋት ትንተና የሚያግዝ መረጃ ማሰባሰብ፤ ማደራጀት እና መተንተን

**አስፈላጊነት/Purpose**

ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች ለስጋት ስራ አመራር በሚጠቅም መልኩ መረጃዎችን በማሰባሰብ ለስጋት ትንተና ግብዓት ለማዋል።

**የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎች**

➢ ተለይተው የተዘጋጁ ስጋቶች፤

➢ የተለዩ የመረጃ ምንጮች፤

➢ የተዘጋጁ መረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎች (በሲስተም ወይም በማኑዋል)

### የአፈፃፀም ቅደም ተከተል/ Procedures

- ተለይተው የተቀመጡ ስጋቶችን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ የቅድመ-ማጣራት ሥራ ማከናወን፤
- የሥራ ቅደም ተከተል ማዘጋጀት፤
- ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች መረጃ ማሰባሰብ፡-
  - በሲስተም የሚያዙ የሪከርድ መረጃዎች ከጉምሩክ ዳታ ቤዝ(አሲኩዳ)፣ ከስጋት ስራ አመራር ዳታ ቤዝ(TPRDP)፣ ECVS፣ VDD፣ SINGLE WINDOW ወዘተ፣
  - በማኑዋል የሚያዙ ሪከርዶች ከተለያዩ የስራ ክፍሎች ከሚያዙ መረጃዎች (ከፍተሻ፣ ከድንገተኛ ፍተሻ፤ ከኢንተለጀንስ፤ ከድህረ-ዕቃ አወጣጥ ኦዲት፣ ከፓትሮሊንግ እና ኮንትሮባንድ ክትትል፣ ከሶስተኛ ወገን ወዘተ የሚገኝ መረጃ)
  - ከውጭ የሚሰበሰቡ መረጃዎች ከምርመራ፤ ከአቃቤ ህግ፤ ከተጓዳኝ መ/ቤቶች (ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እና በስሩ ካሉ ተጠሪ ተቋማት፣ የደረጃዎች ኤጀንሲ)፣ ከባትሎአድ፣ ከኢንዱስትሪ ሚ/ር፣ ከንግድ ሚ/ር፤ ከትራንስፖርት ሚ/ር፣ ከባንክ እና ከኢንሹራንስ ወዘተ ይሆናል፡፡

## 2.1.4. አራተኛ ደረጃ፡- ስጋትን መተንተን እና የስጋት ደረጃ ማውጣት፤

### የተግባር መግለጫ

ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች በተሰበሰቡ መረጃዎች መሰረት ስጋቶችን መተንተን እና የስጋት ደረጃ ማውጣት፤

### አስፈላጊነት/Purpose

በየወቅቱ ሊከሰቱ የሚችሉ ስጋቶችን በብቃት በመለየት ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች የተሰበሰቡ መረጃዎች ስጋቶችን በመተንተንና ደረጃ በማውጣት ለውሳኔ በሚጠቅም መልኩ ማዘጋጀት፤

### የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎች

- የተደራጀና የጠራ መረጃ፤
- የሥጋት ሥራ አመራር መሰረታዊ ክህሎት፤
- የሥጋት ሥራ አመራር ፖሊሲና ስትራቴጂ፤

➢ ተለይተው የተቀመጡ የስጋት ትንታኔ/መስፈርቶች

**የአፈፃፀም ቅደም ተከተል/ Procedures**

➢ መመዘኛ መስፈርቶችን በመጠቀም ስጋቶችን መተንተን እና የስጋት ደረጃ ማውጣት፤

- ትንተና የሚከናወነው በሥጋት ስራ አመራር ፖሊሲና ስትራቴጂ ላይ በተቀመጠው ቀመር መሰረት ስጋት የመከሰት ዕድልና ስጋቱ የሚያስከትለው ተጽኖ በማስላት ሲሆን ትንተናውን ለማከናወን ፖሊሲውን መሰረት በማድረግ የሥጋት ደረጃዎች እንደሚከተለው የሚወሰኑ ይሆናል፡-
  - ✓ ***ሥጋት የመከሰት ዕድል*** (likelihood)፡- ማለት ቀደም ካሉ መረጃዎች በመነሳት ወደፊት ስጋት የመከሰት እድሉን የምንለካበት ሲሆን በፖሊሲው መሰረት ሥጋት የመከሰት እድል በሶስት ደረጃዎች የተከፋፈለ ነው። ለምሳሌ እነዚህ ደረጃዎች ይህ ማኑዋሉ ሲሻሻል በነበረው ስሌት፡-
    - *ሥጋት የመከሰት እድል ቀመር* (likelihood)[1] 10% እና ከ10% በታች ከሆነ ዝቅተኛ የስጋት ደረጃ /LOW RISK,
    - *ሥጋት የመከሰት እድል ቀመር* ከ10% በላይ እና 20% እና ከ 20% በታች ከሆነ፣ መካከለኛ የስጋት ደረጃ /MEDIUM RISK,
    - *ሥጋት የመከሰት እድል ቀመር ከ* 20% በላይ ከሆነ፣ ከፍተኛ የስጋት ደረጃ/HIGH RISK ይሆናል።
  - ✓ **የተከሰተው ስጋት የሚያስከትለው ተጽዕኖ**(CONSEQUENCE)፡- ማለት ቀደም ካሉ መረጃዎች በመነሳት ወደፊት ስጋት ቢከሰት የሚያስከትለውን ተጽዕኖ የምንለካበት ሲሆን በፖሊሲው መሰረት ስጋቱ የሚያስከትለው ተጽዕኖ (CONSEQUENCE) በሶስት ደረጃዎች የተከፋፈለ ነው። እነሱም፡-
    - ስጋቱ የሚያስከትለው ተጽኖ ቀመር 5% እና ከ 5% በታች ከሆነ፣ ዝቅተኛ የስጋት ደረጃ/LOW RISK,
    - ስጋቱ የሚያስከትለው ተጽዕኖ ቀመር ከ5% በላይ እና 7.5% እና ከ 7.5% በታች ከሆነ መካከለኛ የስጋት ደረጃ/MEDIUM RISK,
    - ስጋቱ የሚያስከትለው ተጽዕኖ ቀመር ከ7.5% በላይ ከሆነ፣ ከፍተኛ የስጋት ደረጃ/HIGH RISK ይሆናል።

---

በመጨረሻም ሥጋት የመከሰት እድል (Likelihood) እና ሥጋቱ የሚያስከትለው የኢኮኖሚ እና ማህበራዊ ተጽዕኖ (Consequence) ጥምርታ (Matrix) በመሥራት በሚከተለው ሰንጠረዥ በተቀመጠው መልኩ የመጨረሻው የሥጋት ደረጃ ይወሰናል።

ሥጋት የመከሰት እድል/Likelihood

| | | | |
|---|---|---|---|
| ከፍተኛ | መካከለኛ | ከፍተኛ | ከፍተኛ |
| መካከለኛ | ዝቅተኛ | መካከለኛ | ከፍተኛ |
| ዝቅተኛ | ዝቅተኛ | ዝቅተኛ | መካከለኛ |
| | ዝቅተኛ | መካከለኛ | ከፍተኛ |

የሚያስከትለው ተጽዕኖ/Consequence

ሥጋት የመከሰት እድል ቀመር (likelihood) እና ስጋቱ የሚያስከትለው ተጽዕኖ (CONSEQUENCE) ቀመር እና ጥምርታ (Matrix) በየጊዜው በስጋት ስራ አመራር ኮሚቴው ውሳኔ መሰረት በሚደረጉ ማሻሻያዎች ሊቀያየር ይችላል።

ለምሳሌ፦ የአንድ አስመጪ ስጋት ለመለካት

አጠቃላይ በሶስት ዓመት ውስጥ የማስመጣት ድግግሞሽ በሰነድ ቁጥር=20

በሶስት ዓመት ውስጥ ልዩነት የተገኘባቸው ሰነዶች ቁጥር=3

በሶስት ዓመት ውስጥ አጠቃላይ የተከፈለ ቀረጥ እና ታክስ=2,000,000

በሶስት ዓመት ውስጥ በልዩነት የተሰበሰበ ቀረጥ እና ታክስ=450,000

የመከሰት እድል= <u>ልዩነት የተገኘባቸው ሰነዶች ቁጥር*</u> *100 = 3/20*100=15%=መካከለኛ
አጠቃላይ የማስመጣት ድግግሞሽ በሰነድ ቁጥር

የሚያስከትለው ተጽዕኖ= <u>አጠቃላይ የተከፈለ ቀረጥ እና ታክስ</u>100= <u>450,000</u> *100=22.5%=ከፍተኛ
በልዩነት የተሰበሰበ ቀረጥ እና ታክስ 2,000,000

የመጨረሻው የአስመጪው የስጋት ደረጃ በጥምርታው መሰረት ከፍተኛ ይሆናል ማለት ነው።

ማስታወሻ ፡ በልዩነት የተከፈለው ሲባል የሰነድ ምርመራ ተደርጎ በልዩነት የተከፈለ፣ በድህ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ግኝት ሲኖር የተከፈለ እና ሌሎች ከጥፋት ጋር የተያዩዙ ክፍያዎችን ይጨምራል።

- የስጋት ደረጃ ማውጣት፡- የስጋት መረጃዎች ከተተነተኑ በኋላ የስጋት ደረጃዎች ይወጣሉ፤
- የተተነተኑና የስጋት ደረጃዎች የወጡላቸው መረጃዎች ለውሳኔ ዝግጁ ማድረግና ለተጠቃሚ አካል ማስተላለፍ፤ በቅ/ጽ/ቤቱ የሚገኙ የተለያዩ ስራ ክፍሎች እና የስጋት ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት እንዲሁም ሌሎች ቅ/ጽ/ቤቶች የዚህ ውጤት ተጠቃሚ ይሆናሉ።

## 2.1.5. አምስተኛ ደረጃ፡- *ሥጋትን መመዘን እና ማስተናገድ፤*

### የተግባር መግለጫ

ከላይ ደረጃ አራት ላይ በሚቀመጠው የሥጋት ደረጃ መሰረት ስጋቶችን በመመዘን ስጋቶችን ማስተናገድ

### አስፈላጊነት/Purpose

ሁሉንም ስጋቶችን ማስተናገድ ስለማይቻል የተለዩትን ስጋቶች በመመዘን ትኩረት ሊደረግባቸው የሚገቡትን ብቻ በመለየት ማስተናገድ እና ውስን የሆነውን ሀብት በተገቢው ሁኔታ ጥቅም ላይ ማዋል አስፈላጊ ነው።

### የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎች

- ተለይተው ደረጃ የወጣላቸው ስጋቶች፤

### የአፈፃፀም ቅደም ተከተል/ Procedures

- ተለይተው ደረጃ የወጣላቸውን ስጋቶች መመዘን እና በቅደም ተከተል ማስቀመጥ
- በስጋት ደረጃዎቹ መሰረት የመስተንግዶ ስትራቴጂ ማዘጋጀት
- የመስተንግዶ ስትራቴጂዎቹን ተግባራዊ ማድረግ

# ምዕራፍ ሦስት

## የገቢ ዕቃ አወጣጥ ሥጋት አጣጣል

### 3.1. ስድስተኛ ደረጃ: ስጋትን መጣልና በሲስተም የተጣለ ስጋትን ማሻሻል፤

### 3.1.1. በሲስተም ስጋት መጣል በማይቻልበት ሁኔታ ሥጋትን መጣል፡

**የተግባር መግለጫ**

በሲስተም ሥጋት መጣል የማይቻልበት ሁኔታ ለምሳሌ ሲስተሙ የማይሰራ ከሆነ ወይም መብራት በማይኖርበት ጊዜ ሲስተሙን ተክቶ በማኑዋል የስጋት ደረጃ ይጣላል፤

**አስፈላጊነት/Purpose ፤**

ከላይ በተገለጹት የተለያዩ ምክንያቶች ሲስተሙ የስጋት ደረጃ በማይጥልበት ጊዜ የሚፈጠርን የስራ መስተጓጎል ለማስቀረት፤

**የሚያስፈልገው ጊዜ፤**

አንድን ሰነድ መርምሮ ስጋት ለመጣል ከስጋት አንጻር ተጨማሪ ማጣራት የሚያስፈልገው ካልሆነ በስተቀር 5 ደቂቃ የመወሰኛ ሰዓት ተደረጎ ይወሰዳል።

**የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎች**

- በሲስተም ስጋት ደረጃ ያልተጣለበት ሰነድ፤
- የተደራጀ መረጃና የተተነተነ መረጃ፤
- ሌሎች ተጨማሪ መረጃዎች /ለምሳሌ የኢንተለጀንስ / ካለ /
- የስጋት ስራ አመራር ፖሊሲና ስትራቴጂ፤
- የስጋት ስራ አመራር መሰረታዊ ክህሎት፤

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ... Ethiopian Revenues and Customs Authority Records & Documentation No. 3

## የአፈፃፀም ቅደም ተከተል/ Procedures

- በሲስተም የስጋት ደረጃቸው ያልተጣሉ ሰነዶችን ከፌዝቬት መቀበል፤
- የስጋት ደረጃዎችን ከዚህ በታች (ከሀ እስከ ሐ) በተገለጸው መሰረት መጣል፤

## ፈጻሚ አካል

በቅ/ጽ/ቤቶች የሚገኙ የስጋት ስራ አመራር ባለሙያዎች በተቀመጠላቸው የሥራ መዘርዝር መሰረት የሚፈጽሙት ይሆናል።

ሀ) ሰማያዊ ስጋት ደረጃ የሚስተናገዱ፤

- ታማኝ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ ድርጅቶች ከተሰጣቸው መብት ጋር በተያያዘ የሚያስመጧቸው እቃዎች፤

ለ) በአረንጓዴ ስጋት ደረጃ የሚስተናገዱ፤

- የመንግስት መ/ቤቶችና የመንግስት የልማት ድርጅቶች የሚያስገቧቸው እቃዎች ሆነው በCPC 4000 403፣ 4000 401፣ 4000 410፣ 4000 441፣ 4000 407፣4000 417፣ 4000 418 የመጠቀም መብት ያላቸው ሆነው በራሳቸው ስም ሲያስመጡ፤
- ልዩ የጉምሩክ አገልግሎት ተጠቃሚ ድርጅቶች የሚያስመጧቸው ዕቃዎች (Special Privilege scheme)፤ (በ 'S' የሚመጡ ሰነዶችንም ጨምሮ)፤ ነገር ግን ሰነድ ምርመራ ወይም አካላዊ ፍተሸ ለማድረግ አመላካች ነገሮች ካሉ ወይም በአልፎ አልፎ መረጣ ከተመረጡ በመካከለኛ ወይም በከፍተኛ የስጋት ደረጃ ሊስተናገዱ ይችላሉ።
- መብት ያላቸው ዲፕሎማቶች፤ ኤምባሲዎች፤ ዓለም አቀፍና አህጉር አቀፍ ድርጅቶች የሚያስመጧቸው በCPC 415፣ 416፤ 476፤ 473፤ የሚያስመጧቸው እቃዎች፣
- የኤክስፖርት ማበረታቻ ስርዓት ተጠቃሚ የሆኑ ድርጅቶች የሚያስመጧቸው ዕቃዎች (የሚያስገቡት የምርት ግብዓቶች ከሆነ እና ኤክስፖርት የሚደረጉ ዕቃዎችን በማምረት የተሰማሩ ከሆነ)፤ ነገር ግን አሳማኝ መረጃ ካለ በቀይ የሥጋት ደረጃ ሊስተናገዱ ይችላሉ
- የመንግስት መ/ቤት ለመንግስት መ/ቤት ወኪል /care off/ ሆኖ ዕቃዎችን ሲያስመጣ

ሐ) በቢጫ ስጋት ደረጃ የሚስተናገዱ፣

- ልዩ መብት ያልተሰጣቸው አምራች ድርጅቶች ለማበረታታት በመንግስት ወይም በተቋሙ በወጪ ማበረታቻዎች የሚቀመጠውን የአምራችነት መስፈረት የሚያሟሉ ድርጅቶች የሚያስመጧቸው ዕቃዎች (ያለቀለት ወይም የታሪፍ ለውጥ የማያመጣ ዕቃ የሚያስመጡትን አይጨምርም)፣
- ተመላሽ ኢትዮጵያውያን ዲፕሎማቶች ይዘዋቸው የሚገቡ የግል መገልገያ ዕቃዎች እና የቤት ቁሳቁሶች፣
- ነዳጅና የነዳጅ ውጤቶች፤
- ሁለተኛ መደብ (second schedule) ተጠቃሚ አምራቾች ሲያስመጡ
- በቀላሉ ሊበላሹ የሚችሉ ምግቦች፤ ለፍተሻ ቢንቀሳቀሱ ተሰባሪ የሆኑና ጥንቃቄ የሚሹ ዕቃች(የታሸጉ ምግቦችን እንዲሁም የኤሌክትሮኒክስ ውጤት የሆኑ እና ለረጅም ጊዜ ግልጋሎት ዝግጁ የሆኑ ሌሎች ተሰባሪ ዕቃዎችን አይጨምርም)፤
- የግብርና ግብዓቶች (ኬሚካሎች፣ ዘሮች፣ ማዳበሪያዎች፣ የአረም መርጫ መሳርያዎች) እንዲሁም ለምርምር የሚያገለግሉ የላቦራቶሪ ዕቃዎች፤
- የዓለም አቀፍና አህጉር አቀፍ ድርጅቶች እንዲሁም የኤምባሲ ተሸከርካሪዎች ለሶስተኛ ወገን በሚያስተላልፉበት ጊዜ፤ የስም ዝውውር የሚከናወንባቸው ሰነዶች (ዕቃው ቀድሞ የወጣ ስለሚሆን)
- የኢንቨስትመንትና የፕሮጀክት ማሽነሪዎች ሲመጡ ነገር ግን አሳማኝ መረጃ ካለ በቀይ የስጋት ደረጃ ሊስተናገዱ ይችላሉ።
- በግልጽ ተጭነው የሚመጡ እና በቀላሉ በዓይን በማየት ሊለዩ የሚችሉ ትላልቅ ማሽነሪዎች ሌሎች ለፍተሻ የሚያበቁ የስጋት አመላካቾች ከሌሉ በስተቀር፤ (excavator, drilling machines, lease machines, agricultural machinaries etc)፤
- በመንግስት ልዩ ትኩረት ተሰጥቷቸው በልዩ ሁኔታ ተፈቅዶ በቀረጥ ነጻ መብት በCPC 421 የሚስተናገዱ ዕቃዎች ከሆኑ የመንግስት ትልልቅ ፕሮጀክቶችን ሳይጨምር፤ ነገር ግን አካላዊ ፍተሻ ለማድረግ የሥጋት አመላካች ነገሮች ካሉ በከፍተኛ የሥጋት ደረጃ ሊስተናገዱ ይችላሉ።
- ቦንድድ መጋዘን የተፈቀደላቸው አስመጪዎች ሰነዶቻቸው ከ'S' ወደ 'C' ሲቀየር (በሚቀናነስበት ጊዜ ተጨማሪ ክፍያ ሲኖር ሰነድ መርማሪው እንዲያረጋግጥ)፤

በተደጋጋሚ ሰነዳቸው ተመርምሮ ልዩነት የማይገኝባቸው ድርጅቶች ከላይ የተዘረዘሩት በቢጫ የስጋት ደረጃ ለማስተናገድ እንደ መነሻ የተቀመጡ ሁኔታዎች ቢኖሩም በዝቅተኛ የስጋት ደረጃ ሊስተናገዱ ይችላሉ፡

በተደጋጋሚ ሰነዳቸው ተመርምሮ ልዩነት የሚገኝባቸው ድርጅቶች ከላይ የተዘረዘሩት በቢጫ የስጋት ደረጃ ለማስተናገድ እንደ መነሻ የተቀመጡ ሁኔታዎች ቢኖሩም በከፍተኛ የስጋት ደረጃ ሊስተናገዱ ይችላሉ።

መ) በቀይ ስጋት ደረጃ የሚስተናገዱ፤

- ከላይ በቢጫ እና በአረንጓዴ የሚስተናገዱ እቃዎች ሆነው ከሶስተኛ ወገን የተገኘ መረጃ የተጠናቀረባቸው ዕቃዎች ሲሆኑ፤
- አሳማኝ የሆነ ከፍተኛ የስጋት አመላካች ሁኔታዎች ሲያጋጥም ለምሳሌ የእቃው አገላለጽ (የዕቃው መለኪያ በቁጥር/pcs/ መገለጽ ሲገባው በጥቅል/set/ ሲገለጽ፤ packing list invoice, bill of loading number ወዘተ በሚገባ ገላጭ ሳይሆን ሲቀር)፤
- ሌሎች በሙቀት፣ በቆይታ እና መሰል ምክንያቶች በቀላሉ ሊበላሹ የሚችሉ ምግቦች፤ ለፍተሻ ቢንቀሳቀሱ ተሰባሪ የሆኑና ጥንቃቄ የሚሹ ዕቃዎች በነዚህ እቃዎች ላይ አጠራጣሪ ሁኔታ ሲኖር፤
- ዕቃው ከሌሎች ቅ/ጽ/ቤቶች ወይም የጉምሩክ ኬላዎች እንዲሁም በሌሎች የህግ አካላት ታጅቦ የተላከ ሲሆን፤
- ከሚገባው ዕቃ ጋር በተያያዘ ትኩረት የሚሻ ማስታወሻ/ሪማርክ/ በመንገድ ወረቀቱ ላይ የተጻፈበት ከሆነ (ለምሳሌ የአስመጪ ስም ልዩነት፤ የአምራች ወይም የጉምሩክ ሲል ቁጥር ልዩነት ሲኖር ወዘተ)
- አስመጪው ወይም የጉምሩክ አስተላላፊው በዚህ ማኑዋል በተካተተው የስጋት ድግግሞሽና የሚያስከትለው ተጽዕኖ ስሌት መለኪያ መሰረት በከፍተኛ የስጋት ደረጃ የሚመደቡ ከሆነ፤
- ልዩ መብት የተፈቀደላቸው ድርጅቶች ዘርፉን ከሚገልጽ የአስመጪነት የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የመጨረሻ ኮድ ውጪ ሲያስመጡ፤(ወይም ሌሎች አጠራጣሪ ሁኔታዎች ሲኖሩ)፤

- ቦንድድ መጋዘን የተፈቀደላቸው አስመጪዎች በ'S' ዲክሌር ሲያደርጉ (ነገር ግን ታማኝ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ እና የልዩ የጉምሩክ አገልግሎት ተጠቃሚ ድርጅቶችን ሳይጨምር)፤
- አዲስ አስመጪ ከሆነ (ይህም ሲባል በአጠቃላይ በተስተናገደባቸው ቅ/ጽቤቶች ማስመጣት ከጀመረበት ቀን ጀምሮ ሦስትና ከሦስት ጊዜ በታች ሲያስመጣ አዲስ ሊባል ይችላል፡፡
- የሚገባው ዕቃ ያልተለመደ አዲስ ዕቃ ወይም ከአሁን ቀደም ወደ ሃገር ገብቶ የማያውቅ ከሆነ፤
- ሁለተኛ መደብ (second schedule) ተጠቃሚ አምራቾች በከፊል ያለቀላቸው እቃዎች ሲያስመጡ፤
- የውጭ ፍተሻ የተፈቀደላቸው አስመጪዎች ሆነው፤ የስጋት አመላካች ሁኔታዎች ሲኖሩ (ኤምባሲዎችን እና ያለመፈተሽ መብት ያላቸውን አስመልክቶ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር ግንኙነት በማድረግ የሚከናወን ይሆናል)፤
- በጉምሩክ መጋዘኖች ጉምሩክ ሥነ ሥርዓት የሚፈጸምባቸው ተሽከርካሪዎች (የመንግስትና የልማት ድርጅቶችን ሳይጨምር)፤
- ዕቃው የመጣው በባለቤቱ ሳይሆን በሌላ አስመጪ ከሆነ(care off) ወይም ተጭኖ የመጣው ከሌላ አስመጪ ዕቃ ጋር በአንድ ኮንቴነር ከሆነ፤
- ለኤግዚቪሽን የሚገቡ ዕቃዎች (ዕቃው ተመልሶ ሊወጣ ስለሚችል የሚመጣውን እቃ በሰነድ ማረጋገጥ አስፈላጊ ስለሆነ)፣
- በከፍተኛ ስጋት ደረጃ ከተመደቡ ሀገራት የሚመጡ ዕቃዎች ሆነው በዓይነት፤ በቲክነስ፤ በጥራት፣ በመጠን፣ በብራድ፣ በቀለም ወዘተ መሰረት የሚወሰኑ በዋጋ ማነጻጸርያ ላይ ከተጠቀሱት ዕቃዎች ሲነጻጸሩ ወይም በፖሊሲው የተጽዕኖ መለከያ መሰረት ከፍተኛ የሆነ የዋጋ ልዩነት ሊያስከትሉ የሚችሉ ዕቃዎች ሲሆኑ፤
- ከተጓዳኝ መ/ቤቶች ቅድመ-ሁኔታ ተሟልቶ እንዲስተናገዱ ከተገለጸ (ለምሳሌ ቀረጥ ነጻ ተፈቅዶላቸው ቅድመ-ሁኔታዎች ተረጋግጠው እንዲስተናገዱ የሚጠይቅ ደብዳቤ ሲኖር እና ወ.ዘ.ተ)፤
- በከፍልፋይ ተጓጉዘው የሚመጡ ጭነቶች (partial shipment)፤ AEO፣ የልዩ መብት ተጠቃሚዎች በተፈቀደላቸው ዘርፍ መሰረት፣ መንግስታዊ እና ዲፕሎማቲክ መብት ያላቸውን ሳይጨምር፤

- ቀረጥ የሚከፈልበትና የማይከፈልበት ዕቃ በአንድ ሰነድ ተቀላቅለው ሲመጡ ነገር ግ አጠራጣሪ ሁኔታ ከሌለ በስተቀር AEO እና የልዩ መብት ተጠቃሚዎችን በተፈቀደላቸው ዘርፍ ሲያስመጡ አይጨምርም።
- አህጉራዊና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች፤ ልዩ የጉምሩክ አገልግሎት ተጠቃሚዎች፤ ታማኝ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሾች እና የመንግስት መ/ቤቶችና የመንግስት የልማት ድርጅቶች፣ የቫውቸር፣ ኤክስፖርት ቦንድድ መጋዘን ተጠቃሚ የሆኑ ድርጅቶች ዕቃዎች ሆነው በዝቅተኛ የስጋት ደረጃ ከሚስተናገዱ ድርጅቶች ውጭ በሌላ ስም (በcareoff) ሲመጡ፤
- አህጉራዊና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች፤ ልዩ የጉምሩክ አገልግሎት ተጠቃሚዎች፤ ታማኝ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሾች እና የቫውቸር ኤክስፖርት ቦንድድ መጋዘን ተጠቃሚ የሆኑ ድርጅቶች ሆነው በግለሰብ ስም (careoff) ሲመጣ
- የመንግስት መ/ቤቶችና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ሆነው በግለሰብ ስም (careoff) ሲመጣ
- በአካል የተገኘ የአምራቹ የኮንቴር ቁጥርና የኮንቴነር ሲል ቁጥር በሰነድ ላይ የተጠቀሰው የኮንቴር ቁጥርና የኮንቴነር ሲል ቁጥር ልዩነት ሲኖረው፤
- ለጥገና ወደ ውጪ ወጥቶ በIM6 የሚገቡ ዕቃዎች ሲሆኑ፤
- በሚሚያ እና በምትክነት የሚገቡ ዕቃዎች ሲሆኑ እና ኤክስፖርት ተደርገው በተለያየ ምክንያት(በብልሽት፣ በጥራት መጓደል ወ.ዘ.ተ)፤ ወደ ሀገር ተመልሰው የሚገቡ ዕቃዎች፣
- የሚገቡት ዕቃዎች ያገለገሉ ዕቃዎች (used goods) ከሆኑ ነገር ግን ትላልቅ ማሽነሪዎች ከሆኑ አጠራጣሪ ሁኔታ ከሌለ በስተቀር አይጨምርም፤
- ተሽከርካሪዎች
- 60% እና በላይ ኤክሳይዝ ታክስ የሚጣልባቸው ዕቃዎች (በልዩ ሁኔታ መብቱ ከተሰጣቸው ድርጅቶች ውጪ)፣
- በአንድ ኮንቴነር ሁለት እና ከዚያ በላይ በሆኑ አስመጪዎች ስም ሲመጣ(PART CONTAINER)፤ (በልዩ ሁኔታ መብቱ ከተሰጣቸው ድርጅቶች ውጪ)፤
- በጊዜያዊነት የሚገቡ ዕቃዎች (ዲፕሎማቲክ መብት ካላቸው ውጪ)፤

ከላይ በአረንጓዴ ወይም በቢጫ ወይም በቀይ የሚስተናገዱበት ሁኔታ እንዳለ ሆኖ የተለየ ሁኔታ ካጋጠመ ሰነዱ በቀይ የሥጋት ደረጃ ይስተናገዳል።

ሲስተም በማይኖርበት ጊዜ ለመስተንግዶ ከላይ ከተዘረዘሩት ውጪ ከሆነ በቀይ የስጋት ደረጃ የሚስተናገድ ይሆናል።

በተደጋጋሚ ተፈትሸው ልዩነት የማይገኝባቸው ድርጅቶች ከላይ እንደ መነሻ የተዘረዘሩት ቢኖሩም በመካከለኛ ወይም በዝቅተኛ የስጋት ደረጃ ሊስተናገዱ ይችላሉ። ከላይ እንደተዘረዘረው ሲስተም በማይኖርበት ጊዜ በማኑዋል የሚስተናገዱ ሰነዶችን በተመለከተ፡-

- በአውቶሜሽን ሲስተም ሲሰራ የስጋት ደረጃቸው በድጋሚ እንዲጣል ይደረጋል።
- ሲስተም የጣለው የስጋት ደረጃ በማኑዋል ከተጣለው የስጋት ደረጃ ጋር ልዩነት ሲኖርው በማኑዋል የተጣለው የስጋት ደረጃ ተፈጻሚ ይሆናል።

## 3.1.2. በሲስተም የተጣለን የስጋት ደረጃ በማኑዋል ማሻሻል (manuall Intervention)፤

### የተግባር መግለጫ

- በአውቶሜሽን በሲስተም የሚጣልን የስጋት ደረጃ በማኑዋል ማሻሻል፤
- ስጋቶችን ለመቀየር ከዚህ በታች (ከሀ እስከ ሽ) በተገለጸው መሰረት ይሻሻላል፤

### አስፈላጊነት/Purpose

በአሲኩዳ++ በአውቶሜሽን በሲስተም የሚጣል የስጋት ደረጃ ወቅታዊ የሆኑ ነባራዊ ሁኔታዎችን /Real Time situation/ እና የሚፈጠሩ ስጋቶችን ግምት ውስጥ ማስገባት ስለማይችል በተጨማሪም ስርዓቱ ቀድሞ ተተንትኖ በሚገኝ ውጤት ላይ/ Pre-defined rules/ መሰረት የሚሰራ በመሆኑ እና መሰል ክፍተቶችን እንደችግሩ ነባራዊ ሁኔታ ለማስተዳደር በሲስተም የተጣለን ስጋት ጥራት መከታተልና በማኑዋል መሻሻያዎችን ማድረግ በማስፈለጉ ነው።

### የሚያስፈልገው ጊዜ፤

አንድን ሰነድ መርምሮ ስጋት ለመጣል ከስጋት አንጻር ተጨማሪ ማጣራት የሚያስፈልገው ካልሆነ በስተቀር 3 ደቂቃ የመወሰኛ ሰዓት ተደርጎ ይወሰዳል።

### የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎች

- ➢ በሲስተም የሥጋት ደረጃ የተጣለበት ሰነድ፤
- ➢ የተደራጀ መረጃና የተተነተነ የሥጋት ደረጃ፤
- ➢ የሥጋት ሥራ አመራር ፖሊሲና ስትራቴጂ፤
- ➢ የሥጋት ሥራ አመራር መሰረታዊ ክህሎት፤

### የአፈፃፀም ቅደም ተከተል/ Procedures

- ➢ በሲስተም የስጋት ደረጃቸው የተጣሉ ሰነዶችን ከፌዝቤት መቀበል፤
- ➢ ስጋቶችን ከዚህ በታች (ከሀ እስከ ሸ) በተገለጸው መሰረት ማሻሻል፤

### ፈጻሚ አካል

- ➢ በቅ/ጽ/ቤቶች የሚገኙ የሥጋት ሥራ አመራር ባለሙያዎች በተቀመጠላቸው የሥራ መዘርዝር መሠረት የሚፈጽሙት ይሆናል።

### ሀ) ከቢጫ ወይም ከቀይ ወይም ከአረንጓዴ ወደ ሰማያዊ ማሻሻል፤ (AEO)

በአውቶሜሽን ሲስተም የጣለው ስጋት ደረጃ ከቢጫ ወይም ቀይ ወይም ከአረንጓዴ ወደ ሰማያዊ በቀጥታ ማሻሻል የሚቻለው የሚከተው ሁኔታ ሲሟላ ነው።

- በተመረጡ ታማኝ የኢኮኖሚ እንቀሳቃሽነት መብት በተሰጣቸው ድርጅቶች (AEO) ከተሰጣቸው መብት ጋር በተያያዘ የሚገቡ ዕቃዎች፤ (በ 'S' የሚመጡ ሰነዶችንም ጨምሮ)፤

ለ) ከቢጫ ወደ አረንጓዴ ማሻሻል፤

በአውቶሚሽን ሲስተም የጣለው ስጋት ደረጃ ቢጫ ሆኖ ወደ አረንጓዴ በቀጥታ ማሻሻል የሚቻለው የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲሟሉ ነው፡፡

- ልዩ የጉምሩክ አገልግሎት ተጠቃሚ ድርጅቶች የሚያስመጧቸው ዕቃዎች (Special Privilege scheme)፤ (በ'S' የሚመጡ ሰነዶችንም ጨምሮ)፤ ነገር ግን ሰነድ ምርመራ ለማድረግ አመላካች ነገሮች ካሉ ሲስተሙ በጣለው የስጋት ደረጃ ሊፀና ይችላል፡፡
- የመንግስት መ/ቤቶችና የመንግስት የልማት ድርጅቶች የሚያስገቧቸው እቃዎች ሆነው በCPC 4000 403፣ 4000 401፣ 4000 410፣ 4000 441፣ 4000 407፣4000 417፣ 4000 418 የመጠቀም መብት ያላቸው ሆነው በራሳቸው ስም ሲያስመጡ፤ ነገር ግን ሰነድ ምርመራ ለማድረግ አመላካች ነገሮች ካሉ ሲስተሙ በጣለው የስጋት ደረጃ ሲፀና ይችላል፡፡
- ዲፕሎማቶች፣ኤምባሲዎችና ዓለም አቀፍ እና አህጉር አቀፍ ድርጅቶች በCPC 415፣ 416፤ 476፤ 473፤ የሚያስመጧቸው እቃዎች
- የኤክስፖርት ማበረታቻ ስርዓት ተጠቃሚ የሆኑ ድርጅቶች የሚያስመጧቸው ዕቃዎች (የሚያስገቡት የምርት ግብዓቶች ከሆኑ እና ኤክስፖርት የሚደረጉ ዕቃዎችን በማምረት የተሰማሩ ከሆነ)፤

ከላይ የተዘረዘሩት ከቢጫ ወደ አረንጓዴ ለመቀየር እንደ መነሻ የተቀመጡት ሁኔታዎች ቢኖሩም ከአሁን ቀደም ተፈትሸው ወይም ሰነዳቸው ተመርምሮ ልዩነት የሚገኝባቸው ድርጅቶች ከሆኑ፣ የስጋት አመላካቾች ካሉ ወይም በአልፎ አልፎ መረጣ ከተመረጡ (ያለመፈተሽ መብት ያላቸውን ሳይጨምር) ሲስተሙ በጣለው በመካከለኛ ወይም በከፍተኛ የስጋት ደረጃ ሊስተናገዱ ይችላሉ፡፡

ሐ) ከቀይ ወደ አረንጓዴ ማሻሻል፤

በአውቶሚሽን ሲስተም የጣለው ስጋት ደረጃ ቀይ ሆኖ ወደ አረንጓዴ በቀጥታ ማሻሻል የሚቻለው የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲሟሉ ነው፡፡

- ልዩ የጉምሩክ አገልግሎት ተጠቃሚ ድርጅቶች የሚያስመጧቸው ዕቃዎች (Special Privilege scheme)፤ (በ 'S' የሚመጡ ሰነዶችንም ጨምሮ)፤ ሆኖም ግን ለፍተሻ



Ethiopian Revenues and Customs Authority Records & Documentation No. 7

የሚያበቁ ተጨማሪ መረጃዎች ካሉ እና በድንገተኛ መረጣ እንዲፈተሹ ከተመረ[illegible] ሲስተም የጣለው የስጋት ደረጃ ይፀናል።

- የመንግስት መ/ቤቶችና የመንግስት የልማት ድርጅቶች የሚያስገቧቸው እቃዎች ሆነው በCPC 4000 403፣ 4000 401፣ 4000 410፣ 4000 441፣ 4000 407፣4000 417፣ 4000 418 የመጠቀም መብት ያላቸው ሆነው በራሳቸው ስም ሲያስመጡ ሆኖም ግን በነዚህ ዕቃዎች ዙሪያ ለፍተሻ የሚያበቁ ተጨማሪ መረጃዎች ካሉ ሲስተም የጣለው የስጋት ደረጃ ይፀናል።
- ዲፕሎማቶች፣ ኢምባሲዎችና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች በCPC 415፣ 416፣ 476፣ 473፣ የሚያስመጧቸው እቃዎች ሆኖም ግን በነዚህ ዕቃዎች ዙሪያ ለፍተሻ ተጨማሪ መረጃዎች ካሉ የውጭ ጉዳይ ሚ/ር ተወካይ እና ዲፕሎማቱ ወይም የዲፕሎማቱ ተወካይ ባለበት ሊፈተሽ ይችላል።
- የኤክስፖርት ማበረታቻ ሥርዓት ተጠቃሚ የሆኑ ድርጅቶች የሚያስመጧቸው ዕቃዎች (የሚያስገቡት የምርት ግብዓቶች ከሆኑ እና ኤክስፖርት የሚደረጉ ዕቃዎችን በማምረት የተሰማሩ ከሆን)፤

በተደጋጋሚ ተፈትሸው ወይም ሰነዳቸው ተመርምሮ ልዩነት የሚገኝባቸው ድርጅቶች ከላይ የተዘረዘሩት ከቀይ ወደ አረንጓዴ ለመቀየር እንደ መነሻ የተቀመጡት ሁኔታዎች ቢኖሩም ሲስተሙ በሚጥለው በከፍተኛ ወይም በመካከለኛ የስጋት ደረጃ ሊስተናገዱ ይችላሉ (ዲፕሎማቶች፣ ኢምባሲዎችና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ውጪ)።

**መ) ከአረንጓዴ ወደ ቢጫ የሚሻሻሉ፤**

በአውቶሜሽን ሲስተም የጣለው ስጋት ደረጃ አረንጓዴ ሆኖ ወደ ቢጫ በቀጥታ ማሻሻል የሚቻለው የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲሟሉ ነው።

- ቦንድድ መጋዘን የተፈቀደላቸው አስመጪዎች ሰነዶቻቸው ከ'S' ወደ 'C' ሲቀየር (በሚቀናነስበት ጊዜ ተጨማሪ ክፍያ ሲኖር ሰነድ መርማሪው እንዲያረጋግጥ)፤
- ተመላሽ ኢትዮጵያውያን ዲፕሎማቶች ይዘዋቸው የሚገቡ የግል መገልገያ ዕቃዎች እና የቤት ቁሳቁሶች ይዘው ሲመጡ መኪናን አይጨምርም፣ ነገር ግን አሳማኝ መረጃ ካለ ከስራ አስኪያጁ ወይም ከሥራ ሂደት ጋር በመነጋገር ሊፈተሹ ይችላሉ።

- በግልጽ ተጭነው የሚመጡ እና በቀላሉ በዓይን በማየት ሊለዩ የሚችሉ ትላልቅ ማሽነሪዎች ሆነው አጠራጣሪ ሁኔታዎች ሲኖሩ በሰነድ ማረጋገጥ ብቻ በቂ ከሆነ (excavator, drilling machines, lease machines, agricultural machinaries etc)፤
- የዓለም አቀፍና አህጉር አቀፍ ድርጅቶች እንዲሁም የኤምባሲ ተሽከርካሪዎች በሚመጡበት ጊዜ አጠራጣሪ ሁኔታዎች ሲኖሩ፤
- የዓለም አቀፍና አህጉር አቀፍ ድርጅቶች እንዲሁም የኤምባሲ ተሽከርካሪዎች ለሶስተኛ ወገን በሚያስተላልፉበት ጊዜ እንዲሁም ሌሎች የስም ዝውውር የሚከናወንባቸው ሠነዶች
- የኢንቨስትመንትና የፕሮጀክት ማሽነሪዎች ሲመጡ ነገር ግን አሳማኝ መረጃ ካለ በቀይ የሥጋት ደረጃ ሊስተናገዱ ይችላሉ
- የልዩ መበት ተጠቃሚ ያልሆኑ አምራች ድርጅቶች የሚያስመጧቸው ለፋብሪካ ምርት ግብዓት የሚሆኑ ዕቃዎች ሲመጡ፤ ነገር ግን አሳማኝ መረጃ ካለ በቀይ የሥጋት ደረጃ ሊስተናገዱ ይችላሉ
- ኬሚካሎች፣ መድኃኒቶች፤ በቀላሉ ሊበላሹ የሚችሉ ልዩ ልዩ ዕቃዎች (ዋጋቸው በመጠንና በውፍረት(Thickness) የሚወሰኑትን ሳይጨምር ለምሳሌ እንደ ሴራሚ)፣ የህክምና መገልገያ መሳሪያ እና ምግቦች (በቀላሉ የማይበላሹ የታሸጉ ምግቦችን እንዲሁም በዋናነት ለህክምና ተብለው ያልተመረቱ ምርቶችን ሳይጨምር)፤
- ብረታ ብረቶች (ክብደት እየተረጋገጠ የሚስተናገዱ ስለሆነ)
- ተቀጣጣይ (explosive goods) እና ጨረር አመንጪ ዕቃዎች በሚመጡበት ጊዜ አጠራጣሪ ሁኔታዎች ሲኖሩ (ሌሎች በሰነድ የሚረጋገጡ ነገሮችን ለማረጋገጥ)፤
- ሌሎች በሙቀት፣ በቆይታ እና መሰል ምክንያቶች በቀላሉ ሊበላሹ የሚችሉ ምግቦች፤ ለፍተሻ ቢንቀሳቀሱ ተሰባሪ የሆኑና ጥንቃቄ የሚሹ ዕቃች ሆነው አጠራጣሪ ሁኔታዎች ሲኖሩ ሰነዳቸውን አረጋግጦ ማስተናገድ ተገቢ ስለሆነ፤ (የታሸጉ ምግቦችን እንዲሁም የኤሌክትሮኒክስ ውጤት የሆኑ እና ለረጅም ጊዜ ግልጋሎት ዝግጁ የሆኑ ሌሎች ተሰባሪ የሚባሉ ዕቃዎችን ሳይጨምር)

በተደጋጋሚ ሰነዳቸው ተመርምሮ ልዩነት የማይገኝባቸው ድርጅቶች ከላይ የተዘረዘሩት ከአረንጓዴ ወደ ቢጫ ለመቀየር እንደ መነሻ የተቀመጡ ሁኔታዎች ቢኖሩም ሲስተሙ በሚጥለው በዝቅተኛ የስጋት ደረጃ ሊስተናገዱ ይችላሉ፡



Ethiopian Revenues and Customs Authority Records & Documentation

በተደጋጋሚ ሰነዳቸው ተመርምሮ ልዩነት የሚገኝባቸው ድርጅቶች ከላይ የተዘረዘሩት ከአረንጓ ወደ ቢጫ ለመቀየር እንደ መነሻ የተቀመጡ ሁኔታዎች ቢኖሩም አሳማኝ መረጃ ካለ በከፍተኛ የስጋት ደረጃ ሊስተናገዱ ይችላሉ።

ሠ) ከቀይ ወደ ቢጫ የሚሻሻሉ፤

በአውቶሜሽን ሲስተም የጣለው ስጋት ደረጃ ቀይ ሆኖ ወደ ቢጫ በቀጥታ ማሻሻል የሚቻለው የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲሟሉ ነው።

- በመንግስት ልዩ ትኩረት ተሰጥቷቸው በልዩ ሁኔታ ተፈቅዶ በቀረጥ ነጻ መብት በCPC 421 የሚስተናገዱ ዕቃዎች ከሆኑ፤ ነገር ግን ለፍተሻ የሚያበቁ ተጨማሪ መረጃዎች ካሉ እና አልፎ አልፎ መረጣ (Random Selection) እንዲፈተሹ ከተመረጡ ሲስተም የጣለው የስጋት ደረጃ ይፀናል።
- ተመላሽ ኢትዮጵያውያን ዲፕሎማቶች ይዘዋቸው የሚገቡ የግል መገልገያ ዕቃዎች እና የቤት ቁሳቁሶች መኪናን ሳይጨምር፣ ነገር ግን ለፍተሻ አሳማኝ መረጃ ካለ ከሥራ አስኪያጁ ወይም ከሥራ ሂደቱ ጋር በመነጋገር ሊፈተሹ ይችላሉ።
- ቦንድድ መጋዘን የተፈቀደላቸው አስመጪዎች ሰነዶቻቸው ከ'S' ወደ 'C' ሲቀየር (በሚቀናነስበት ጊዜ ተጨማሪ ክፍያ ሲኖር በሰነድ ምርመራ መረጋገጥ የሚችል ስለሆነ)፤
- በግልጽ ተጭነው የሚመጡ እና በቀላሉ በዓይን በማየት ሊለዩ የሚችሉ ትላልቅ ማሽነሪዎች፤ (excavator, drilling machines, lease machines, agricultural machinaries etc) ነገር ግን በነዚህ ዕቃዎች ዙሪያ ለፍተሻ የሚያበቁ ተጨማሪ መረጃዎች ካሉ እና አልፎ አልፎ መረጣ (Random Selection) ይፈተሽ ተብለው ከተለዩ ሲስተም የጣለው የስጋት ደረጃ ይፀናል።
- የዓለም አቀፍና አህጉር አቀፍ ድርጅቶች እንዲሁም የኤምባሲ ተሽከርካሪዎች ለሶስተኛ ወገን በሚያስተላልፉበት ጊዜ (መኪናው ቀድሞ የወጣ ስለሆነ)፤
- የኢንቨስትመንትና የፕሮጀክት ማሽነሪዎች ሲመጡ ነገር ግን አሳማኝ መረጃ ካለ ሲስተም የጣለው የስጋት ደረጃ ይፀናል።

- የልዩ መብት ተጠቃሚ ያልሆኑ አምራች ድርጅቶች የሚያስመጧቸው ለፋብሪካ ምርት ግብዓት የሚሆኑ ዕቃዎች ሲመጡ ነገር ግን አሳማኝ መረጃ ካለ ሲስተም የጣለው የስጋት ደረጃ ይፀናል፡፡
- የስም ዝውውር የሚከናወንባቸው ሰነዶች (ዕቃው ከጉምሩክ ለነፃ ዝውውር ተለቆ ሀገር ውስጥ ገብቶ ግልጋሎት ሲሰጥ የቆየ በመሆኑ)፤
- ኬሚካሎች፣ መድኃኒቶች፤ በቀላሉ ሊበላሹ የሚችሉ ልዩ ልዩ ዕቃዎች (ዋጋቸው በመጠንና በውፍረት(Thickness) የሚወሰኑትን ለምሳሌ እንደ ሴራሚክ ያሉትን ሳይጨምር)፣ የህክምና መገልገያ መሳርያዎችና ምግቦች (በቀላሉ የማይበላሹ የታሸጉ ምግቦችን እንዲሁም በዋናነት ለህክምና ተብለው ያልተመረቱ ምርቶችን ሳይጨምር)፤ ነገር ግን በነዚህ ዕቃዎች ዙሪያ ለፍተሻ የሚያበቁ ተጨማሪ መረጃዎች ካሉ እና አልፎ አልፎ መረጣ Random Selection) ይፈተሽ ተብለው ከተለዩ ሲስተም የጣለው የስጋት ደረጃ ይፀናል፡፡
- ብረታ ብረቶች (ክብደት እየተረጋገጠ የሚስተናገዱ ስለሆነ) ነገር ግን በነዚህ ዕቃዎች ዙሪያ ለፍተሻ የሚያበቁ ተጨማሪ መረጃዎች ካሉ እና በአልፎ አልፎ መረጣ (Random Selection) ይፈተሽ ተብለው ከተለዩ ሲስተም የጣለው የስጋት ደረጃ ይፀናል፡፡
- ተቀጣጣይ (explosive goods) እና ጨረር አመንጪ ዕቃዎች (ዕቃዎቹ ለመፈተሽ አደገኛ ስለሆኑ) ነገር ግን ጥርጣሬ ካለ ከዕቃው ጋር ሊደረጉ የሚገባቸውን የጥንቃቄ መመሪያዎችን በመከተል መታየት የሚችሉ የእቃው አካላት እንዲፈተሹ ሊደረግ ይችላል፤
- ሌሎች በሙቀት፣ በቆይታ እና መሰል ምክንያቶች በቀላሉ ሊበላሹ የሚችሉ ምግቦች፤ ለፍተሻ ቢንቀሳቀሱ ተሰባሪ የሆኑና ጥንቃቄ የሚሹ ዕቃች ከሆኑ( ነገር ግን የታሸጉ ምግቦችን እንዲሁም የኤሌክትሮኒክስ ውጤት የሆኑ እና ለረጅም ጊዜ ግልጋሎት ዝግጁ የሆኑ ሌሎች ተሰባሪ የሚባሉ ዕቃዎችን አይጨምርም)፤

ከላይ የተዘረዘሩት ከቀይ ወደ ቢጫ ለመቀየር እንደ መነሻ የተቀመጡ ሁኔታዎች ቢኖሩም በተደጋጋሚ ሰነዳቸው ተመርምሮ ወይም ተፈተሸው ልዩነት የማይገኝባቸው ድርጅቶች በዝቅተኛ የስጋት ደረጃ ሊስተናገዱ ይችላሉ፡፡

በተደጋጋሚ ተፈትሸው ወይም ሰነዳቸው ተመርምሮ ልዩነት የሚገኝባቸው ድርጅቶች በተመለከተ ከላይ የተዘረዘሩት ከቀይ ወደ ቢጫ ለመቀየር እንደ መነሻ የተቀመጡት ቢኖሩም ሲስተም የጣለው የስጋት ደረጃ ይፀናል።

ረ) ከአረንጓዴ ወደ ቀይ የሚሻሻሉ፤

ከአረንጓዴ ስጋት ደረጃ የተመረጡ ሰነዶች በቀጥታ ወደ ከፍተኛ ስጋት ደረጃ ማሻሻል የሚቻለው ቀጥለው ከተዘረዘሩት ነጥቦች ቢያንስ አንዱን ሲያሟላ ነው።

- በከፍተኛ ስጋት ደረጃ ከተመደቡ ሀገራት የሚመጡ ዕቃዎች ሆነው በዓይነት፤ በውፍረት(Thickness)፤ በጥራት፣ በመጠን፣ በብራድ፣ በቀለም ወዘተ መሠረት የሚወሰኑ በዋጋ ማነጻጸሪያ ላይ ከተጠቀሱ ዕቃዎች ሲነጻጸሩ ወይም በፖሊሲው የተጽዕኖ መለኪያ መሠረት ከፍተኛ የሆነ የዋጋ ልዩነት ሊያስከትሉ የሚችሉ ዕቃዎች ሲሆኑ፤
- አዲስ አስመጪ ከሆነ (ይህም ሲባል በአጠቃላይ በተስተናገደባቸው ቅ/ጽቤቶች ማስመጣት ከጀመረበት ቀን ጀምሮ ሦስትና ከሦስት ጊዜ በታች ሲያስመጣ አዲስ ሊባል ይችላል። ይሁን እንጂ ከላይ በአረንጓዴ የሚስተናገዱ ተብለው ከተጠቀሱት ውጪ መሆን ይኖርበታል)፣
- የሚገባው ዕቃ ያልተለመደ አዲስ ዕቃ ወይም ከአሁን ቀደም ወደ ሀገር ገብቶ የማያውቅ ከሆነ፤
- ቦንድድ መጋዘን የተፈቀደላቸው አስመጪዎች በ'S' ዲክለር ሲያደርጉ (ነገር ግን ታማኝ የኢኮኖሚ እንቀሳቃሽ እና የልዩ የጉምሩክ አገልግሎት ተጠቃሚ ድርጅቶችን ሳይጨምር)፤
- አስመጪው በመረጃ ቋት (TPRDP System) እና በማንዋል በሚያዙ መረጃዎች መሰረት በተደጋጋሚ የፍተሻ ልዩነት የተያዘበት ሲሆን እና ስጋት ደረጃው በሲስተም ካልተሻሻለ፤
- ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች የተገኘ መረጃ (ጥቆማ) ሲኖር/ለምሳሌ ከሶስተኛ ወገን፤
- ልዩ መብት የተሰጣቸውና ታማኝ የኢኮኖሚ እንቀሳቃሽ ድርጅቶች/AEO እዲሁም የቫውቸር፣ የኤክስፖርት ቦንድድ መጋዘን ተጠቃሚዎች፣ ኬሚካሎች፣ መድኃኒቶች፤ በቀላሉ ሊበላሹ የሚችሉ ልዩ ልዩ ዕቃዎች በሲስተም በአረንጓዴ/ቢጫ ስጋት

ከሚስተናገዱ ሰነዶች ውስጥ አምስት በመቶውን (5%) ወደ ከፍተኛ ስጋት ደረጃ በመቀየር ድንገተኛ ፍተሻ (surprise checking) እንዲከናወንበት ማድረግ፤ (ሲስተም የሚጥለው እልፎ አልፎ መረጣ (Random Selection) ከአጠቃላይ አስመጪዎች በመሆኑ የእያንዳንዱን አስመጪ የህግ ተገዥነት ደረጃ ለማወቅና አዳዲስ ስጋቶችን ለመለየት በቂ ስላልሆነ፤ ይህም ሲባል የስጋት ስራ አመራር አፈስሩ አጠራጣሪ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙት እና ሌሎች ጥቆማዎች ሲደርሱት እንዲሁም እንደየ ቅ/ጽ/ቤቱ ነባራዊ ሁኔታ እነዚህን ድርጅቶች መፈተሽ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ቅድሚያ በመስጠት ለመፈተሽ ይረዳ ዘንድ የተቀመጠ ነው)።

- ሁለተኛ መደብ (second schedule) ተጠቃሚ አምራቾች በከፊል ያለቀላቸው እቃዎች ሲያስመጡ፤
- የውጭ ፍተሻ የተፈቀደላቸው አስመጪዎች ሆነው፤ የስጋት አመላካች ሁኔታዎች ሲኖሩ (ኤምባሲዎችን እና ያለመፈተሽ መብት ያላቸውን አስመልክቶ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር ግንኙነት በማድረግ የሚከናወን ይሆናል)፤
- በጉምሩክ መጋዘኖች ጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት የሚፈጸምባቸው ተሽከርካሪዎች (የመንግሥትና የልማት ድርጅቶችን ሳይጨምር)፤
- በጊዚያዊነት የሚገቡ ዕቃዎች (ዲፕሎማቲክ መብት ካላቸው ውጪ)፤
- ለኤግዚቢሽን የሚገቡ ዕቃዎች (ዕቃው ተመልሶ ሊወጣ ስለሚችል የሚመጣውን ዕቃ ማረጋገጥ አስፈላጊ ስለሆነ)፣ ነገር ግን እነዚህ ዕቃዎች እንደአስፈላጊነቱ ቅድሚያ ተሰጥቷቸው ሊስተናገዱ ይችላሉ።
- ከተጓዳኝ መ/ቤቶች ቅድመ-ሁኔታ ተሟልቶ እንዲስተናገዱ ከተገለጸ (ለምሳሌ ቀረጥ ነጻ ተፈቅዶላቸው ቅድመ-ሁኔታዎች ተረጋግጠው እንዲስተናገዱ የሚጠይቅ ደብዳቤ ሲኖር እና ወ.ዘ.ተ)፤
- በከፍልፋይ ተጓጉዘው የሚመጡ ጭነቶች (partial shipment)፤ (ታማኝ የኢኮኖሚ እንቀሳቃሾች/AEO፣ የልዩ መብት ተጠቃሚዎች በተፈቀደላቸው ዘርፍ መሰረት፣ መንግስታዊ እና ዲፕሎማቲክ መብት ያላቸውን ሳይጨምር፤)
- ቀረጥ የሚከፈልበትና የማይከፈልበት ዕቃ በአንድ ሰነድ ተቀላቅለው ሲመጡ (ታማኝ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሾች/AEO እና የልዩ መብት ተጠቃሚዎች በተፈቀደላቸው ዘርፍ ሲያስመጡ አጠራጣሪ ሁኔታ ከሌለ በስተቀር አይጨምርም)፤

* ግለሰብ ለአህጉራዊና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች፤ ልዩ የጉምሩክ አገልግሎ ተጠቃሚዎች፤ ታማኝ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሾች /AEO/ እና የቫውቸር፣ ኤክስፖርት ቦንድድ መጋዘን ተጠቃሚ የሆኑ ድርጅቶች ዕቃ በሌላ ስም (ficareoff) ሲመጣ፤
* ግለሰብ ለመንግስት መ/ቤቶችና ለመንግስት የልማት ድርጅቶች በሌላ ስም (ficareoff) ሲመጣ፤
* በአካል የተገኘ የአምራቹ የኮንቴር ቁጥርና የኮንቴነር ሲል ቁጥር በሰነድ ላይ የተጠቀሰው የኮንቴር ቁጥርና የኮንቴነር ሲል ቁጥር ልዩነት ሲኖረው፤
* ለጥገና ወደ ውጪ ወጥቶ በIM6 የሚገቡ ዕቃዎች ሲሆኑ፤
* በሚሚያ እና በምትክነት የሚገቡ ዕቃዎች ሲሆኑ እና ኤክስፖርት ተደርገው በተለያየ ምክንያት ወደ ሀገር ተመልሰው ሲገቡ (በብልሽት፣ በጥራት መጓደል ወ.ዘ.ተ)፤
* የሚገቡት ዕቃዎች ያገለገሉ ዕቃዎች (used goods) ከሆኑ፤ ነገር ግን ትላልቅ ማሽነሪዎች ከሆኑ አጠራጣሪ ሁኔታ ከሌለ በስተቀር አይጨምርም፤
* ተሸከርካሪዎች (የዓለም አቀፍና አህጉር አቀፍ ድርጅቶች እንዲሁም ኤምባሲዎች ከሚያስመጧቸው ውጪ)፤
* 60% እና ከዚያ በላይ ኤክሳይዝ ታክስ የሚጣልባቸው ዕቃዎች (በልዩ ሁኔታ መብቱ ከተሰጣቸው ድርጅቶች ውጪ)፣
* በአንድ ኮንቴነር ሁለት እና ከዚያ በላይ በሆኑ አስመጪዎች ስም ሲመጣ (PART CONTAINER)፤ (በልዩ ሁኔታ መብቱ ከተሰጣቸው ድርጅቶች ውጪ)፤

በተደጋጋሚ ተፈትሸው እንዲሁም ሰነዳቸው ተመርምሮ ልዩነት የማይገኝባቸውን ድርጅቶች ሲስተሙ በሚጥለው ዝቅተኛ የስጋት ደረጃ ወይም በመካከለኛ የስጋት ደረጃ ሊስተናገዱ ይችላሉ፡፡

ሸ) ከቢጫ ወደ ቀይ የሚሻሻሉ፤

በሲስተም በቢጫ ስጋት ደረጃ የተመረጡ ሰነዶች በቀጥታ ወደ ከፍተኛ የስጋት ደረጃ ማሻሻል የሚቻለው ቀጥለው ከተዘረዘሩት ነጥቦች ቢያንስ አንዱን ሲያሟላ ነው፡፡

* በከፍተኛ ስጋት ደረጃ ከተመደቡ ሀገራት የሚመጡ ዕቃዎች ሆነው በዓይነት፤ በውፍረት(Thickness)፤ በጥራት፣ በመጠን፣ በብራድ፣ በቀለማም ወዘተ መሠረት

የሚወሰኑ በዋጋ ማነጻጸሪያ ላይ ከተጠቀሱ ዕቃዎች ሲነጻጸሩ ከፍተኛ የሆነ የዋጋ ልዩነት ሊያስከትሉ የሚችሉ ዕቃዎች ሲሆኑ፤

- አዲስ አስመጪ ከሆነ (ይህም ሲባል በአጠቃላይ በተስተናገደባቸው ቅ/ጽቤቶች ማስመጣት ከጀመረበት ቀን ጀምሮ ሦስትና ከሦስት ጊዜ በታች ሲያስመጣ አዲስ ሊባል ይችላል ይሁን እንጂ ከላይ በአረንጓዴ የሚስተናገዱ ተብለው ከተጠቀሱት ውጪ መሆን ይኖርበታል)፣
- የሚገባው ዕቃ ያልተለመደ አዲስ ዕቃ ወይም ከአሁን ቀደም ወደ ሀገር ገብቶ የማያውቅ ከሆነ፤
- ቦንድድ መጋዘን የተፈቀደላቸው  አስመጪዎች በ'S' ዲክሌር ሲያደርጉ ታማኝ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ/AEO/ እና የልዩ የጉምሩክ አገልግሎት ተጠቃሚ ድርጅቶችን ሳይጨምር)፤
- የሠነዶች አገላለጽ ለዋጋና ታሪፍ አወሳሰን በሚመች መልኩ ያልቀረበ ሲሆን፤ ወይም በዚህ እና በሌሎች ምክንያቶች ሠነድ መርማሪ ኦፊሰሩ የሥጋት ማሻሻያ ጥያቄ ያቀረበባቸው ሠነዶች፤
- አስመጪው በመረጃ ቋት (TPRDP system) እና በማኑዋል የሚያዙ መረጃዎችን መሠረት በማደረግ በተደጋጋሚ የፍተሻ ልዩነት የተያዘበት ሲሆን፤ ነገር ግን ስጋት ደረጃው በሲስተም ካልተሻሻለ፤
- ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች የተገኘ መረጃ ወይም ጥቆማ ሲኖር፤ ለምሳሌ ከሶስተኛ ወገን፤
- ልዩ መብት የተሰጣቸውና ታማኝ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ ድርጅቶች እዲሁም የቫውቸር፣ የኤክስፖርት ቦንድድ መጋዘን ተጠቃሚዎች፣ ኬሚካሎች፣ መድኃኒቶች፤ በቀላሉ ሊበላሹ የሚችሉ ልዩ ልዩ ዕቃዎች በሲስተም በአረንጓዴ ወይም በቢጫ የስጋት ደረጃ ከሚስተናገዱ ሠነዶች ውስጥ አምስት በመቶ (5%) ወደ ከፍተኛ ስጋት ደረጃ በመቀየር ድንገተኛ ፍተሻ (surprise checking) እንዲከናወንበት ማድረግ፤ (ሲስተም የሚጥለው  እልፎ እልፎ መረጣ (Random Selection) ከአጠቃላይ አስመጪዎች በመሆኑ የእያንዳንዱን አስመጪ የህግ ተገዥነት ደረጃ ለማወቅና አዳዲስ ስጋቶችን ለመለየት በቂ  ስላልሆነ፤ ይህም ሲባል የሥጋት ሥራ አመራር ኦፊሰሩ አጠራጣሪ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙት እና ሌሎች ጥቆማዎች ሲደርሱት

እንዲሁም እንደየ ቅ/ጽ/ቤቱ ነባራዊ ሁኔታ እነዚህን ድርጅቶች መፈተሽ አስፈላጊ ሆ
ሲገኝ ቅድሚያ በመስጠት ለመፈተሽ ይረዳ ዘንደ የተቀመጠ ነው)::

- ሁለተኛ መደብ (second schedule) ተጠቃሚ አምራቾች በከፊል ያለቀላቸው እቃዎች ሲያስመጡ፤
- የውጭ ፍተሻ የተፈቀደላቸው አስመጪዎች ሆነው፤ አጠራጣሪ ሁኔታዎች ሲኖሩ (ኤምባሲዎችን እና ያስመፈተሽ መብት ያላቸውን ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መ/ቤት ጋር ግንኙነት በማደረግ የሚከናወን ይሆናል)፤
- በጉምሩክ መጋዘኖች ጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት የሚፈጸምባቸው ተሽከርካሪዎች (የመንግስትና የልማት ድርጅቶችን ሳይጨምር)፤
- በጊዜያዊት የሚገቡ ዕቃዎች (ዲፕሎማቲክ መብት ካላቸው ውጪ)፤
- ለኤግዚቢሽን የሚገቡ ዕቃዎች (ዕቃው ተመልሶ ሊወጣ ስለሚችል የሚመጣውን ዕቃ ማረጋገጥ አስፈላጊ ስለሆነ)፣ ነገር ግን እነዚህ ዕቃዎች እንደአስፈላጊነቱ ቅድሚያ ተሰጥቷቸው ሊስተናገዱ ይችላሉ።
- ከተንዳኝ መ/ቤቶች ቅድመ-ሁኔታ ተሟልቶ እንዲስተናገዱ ከተገለጸ (ለምሳሌ ቀረጥ ነጻ ተፈቅዶላቸው ቅድመ-ሁኔታዎች ተረጋግጠው እንዲስተናገዱ የሚጠይቅ ደብዳቤ ሲኖር እና ወ.ዘ.ተ)፤
- በክፍልፋይ ተጓጉዘው የሚመጡ ጭነቶች (partial shipment)፤ ታማኝ የኢኮኖሚ እንቀሳቃሽ/AEO/፣ የልዩ መብት ተጠቃሚዎች በተፈቀደላቸው ዘርፍ መሠረት፣ መንግስታዊ እና ዲፕሎማቲክ መብት ያላቸውን ሳይጨምር፤
- ቀረጥ የሚከፈልበትና የማይከፈልበት ዕቃ በአንድ ሰነድ ተቀላቅሰው ሲመጡ፤ ነገር ግን አጠራጣሪ ሁኔታ ከሌለ በስተቀር ታማኝ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ /AEO/ እና የልዩ መብት ተጠቃሚዎችን በተፈቀደላቸው ዘርፍ ሲያስመጡ አይጨምርም፤
- በግለሰብ ስም ለአህጉራዊና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች፤ ለልዩ የጉምሩክ አገልግሎት ተጠቃሚዎች፤ ለታማኝ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሾች/AEO/ ለቫውቸር፣ ለኤክስፖርት ቦንድድ መጋዘን ተጠቃሚ የሆኑ ድርጅቶች ዕቃዎች በሌላ ስም (በcareoff) ሲመጣ፤
- በግለሰብ ስም ለመንግስት መ/ቤቶችና ለመንግስት የልማት ድርጅቶች ዕቃዎች (በcareoff) ሲመጣ፤ ፣
- በአካል የተገኘ የእምራቹ የኮንቴር ቁጥርና የኮንቴነር ሲል ቁጥር በሰነድ ላይ የተጠቀሰው የኮንቴር ቁጥርና የኮንቴነር ሲል ቁጥር ልዩነት ሲኖረው፤

- ለጥገና ወደ ውጪ ወጥቶ በIM6 የሚገቡ ዕቃዎች ሲሆኑ፤
- በሚሚያ እና በምትክነት የሚገቡ ዕቃዎች ሲሆኑ እና ኤክስፖርት ተደርገው በተለያየ ምክንያት (በብልሽት፣ በጥራት መጓደል ወ.ዘ.ተ)፤ ወደ ሀገር ተመልሰው የሚገቡ ዕቃዎች፣
- የሚገቡት ዕቃዎች ያገለገሉ ዕቃዎች (used goods) ከሆኑ ነገር ግን ትላልቅ ማሽነሪዎች ከሆኑ አጠራጣሪ ሁኔታ ከሌለ በስተቀር አይጨምርም፤
- ተሽከርካሪዎች (የዓለም አቀፍና አህጉር አቀፍ ድርጅቶች እንዲሁም ኤምባሲዎች ከሚያስመጧቸው ውጪ)፤
- 60% እና በላይ ኤክሳይዝ ታክስ የሚጣልባቸው ዕቃዎች (በልዩ ሁኔታ መብቱ ከተሰጣቸው ድርጅቶች ውጪ)፣
- በአንድ ኮንቴነር ሁለት እና ከዚያ በላይ በሆኑ አስመጪዎች ስም ሲመጣ(PART CONTAINER)፤ (በልዩ ሁኔታ መብቱ ከተሰጣቸው ድርጅቶች ውጪ)፤

በተደጋጋሚ ተፈትሸው እንዲሁም ሠነዳቸው ተመርምሮ ልዩነት የማይገኝባቸውን ድርጅቶች ሲሰተሙ በሚጥለው በመካከለኛ የስጋት ደረጃ ወይም በዝቅተኛ የስጋት ደረጃ ሊስተናገዱ ይችላሉ።



Ethiopian Revenues and Customs Authority Documentation No. 2

# ምዕራፍ አራት

## የገቢና ወጪ ዕቃዎች ትራንዚት ቁጥጥር (የካርጎ ስካኒንግ ፍተሻ) ስጋት ደረጃ አጣጣል፤

### 4.1. የገቢ ዕቃዎች ትራንዚት ቁጥጥር (የካርጎ ስካኒንግ ፍተሻ) ስጋት ደረጃ አጣጣል፤

**የተግባር መግለጫ**

የገቢ ዕቃዎች ትራንዚት ቁጥጥርን በስጋት ስራ አመራር መሰረት ማከናወን፤

**አስፈላጊነት/Purpose**

የገቢ ዕቃዎች ትራንዚት ቁጥጥር በካርጎ ስካኒንግ መፈተሻ መሳሪያ እየታገዘ በማከናወን ቁጥጥሩን ውጤታማ በሆነ መልኩ ለማረጋገጥ በስጋት ስራ አመራር መሰረት ተግባራዊ ለማድረግ፤

**የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎች**

- በትራንዚት ኢንስፔክተር የተረጋገጠ የመንገድ ወረቀት (T1)፤
- የትራንዚት ዲ/ዮን (IM8)፤
- ትራክ ማንፌስት (እንደ አስፈላጊነቱ)፤
- የተደራጀ የስጋት መረጃ፤
- የስጋት ስራ አመራር መሰረታዊ ክህሎት፤

**የአፈፃፀም ቅደም ተከተል/ Procedures**

- ሰነድ ከትራንዚት ቁጥጥር ባለሙያ መቀበል፤
- ስጋቶችን ከዚህ በታች (ከሀ እስከ ለ) በተገለጸው የሥጋት ደረጃ በመጣል ወደ ሚቀጥለው ስካኒንግ ዩኒት ማስተላለፍ፤

### ፈጻሚ አካል

- ➢ በቅ/ጽ/ቤቶች የሚገኙ የስጋት ስራ አመራር ባለሙያዎች በተቀመጠላቸው የሥራ መዘርዝር መሰረት የሚፈጽሙት ይሆናል።

ሀ) በከፍተኛ (ብርቱካናማ) የስጋት ደረጃ የሚስተናገዱ፤

- ከኢንተለጀንስና ከተለያዩ አካላት ጥቆማ የሚቀርብባቸው፤
- የተረጋጋ የፖለቲካ ስርዓት ከሌላቸው ሀገራት የተመረቱ ወይም የተጫኑ ከሆነ
- በአደንዛዥ ዕጽ ዝውውር ከታወቁ ሀገራት የተጫኑ ከሆነ
- በየቀኑ ከሚመጡት ጭነቶች እልፎ እልፎ መረጣ /Random selection/ አምስት በመቶ (5%) ፤
- በመንገድ ወረቀቱ ላይ የጎረቤት አገር(T1) ወይም IM8 ላይ ሪማርክ የተፃፈ ከሆነ፤
- ዕቃዎች ካላቸው ባህሪ አንጻር የማጭበርበር ድርጊት የሚፈጸምባቸው በየወሩ በፍተሻ እና ሰነድ ምርምራ ሪፖርት የቀረበባቸው አስመጪዎች ወይም የጉምሩክ አስተላላፊዎች የሚያስመጧቸው ጭነቶች፤ /ከTPRDP ወይም ከሌሎች በሲስተም ወይም በማኑዋል ከሚገኙ መረጃዎች/
- በዩኒሞዳል ትርንስፖርት ሲስተም ለሚጓዙ ጭነቶች በሶስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ሶስት እና ከዚያ በላይ የከባድ ጥፋት ሪከርድ ባለባቸው የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አስፈጻሚዎች የሚስተናገዱ ሰነዶች፤ /ከTPRDP ወይም ከሌሎች በሲስተም ወይም በማኑዋል ከሚገኙ መረጃዎች/
- ልዩ የጉምሩክ አገልግሎት ተጠቃሚዎች እና ታማኝ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሾች (AEO) የሚያስመጧቸው ዕቃዎች ከሌሎች ጭነቶች ጋር ተቀላቅለው ሲመጡ፤
- ልዩ መብት የተፈቀደላቸው ድርጅቶች ዘርፉን ከሚገልጽ የአስመጪነት የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የመጨረሻ ኮድ ውጪ ሲያስመጡ፤ (ዕቃው ከተሰማሩበት የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ውጪ ለንግድ ወይም ለሌላ አገልግሎት ስለሚሆን)
- ልዩ መብት የተሰጣቸውና ታማኝ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ ድርጅቶችም በዝቅተኛ ስጋት ከሚስተናገዱ ጭነቶች ውስጥ አምስት በመቶውን ወደ ከፍተኛ ስጋት ደረጃ በመቀየር ድንገተኛ ፍተሻ (surprise checking) እንዲከናወንበት ማድረግ፤

* በሚያዙ የጥፋት መረጃ መሠረት በተደጋጋሚ የአገላለጽና የትርፍ ልዩነት የሚገኝባቸ ድርጅቶች ሲያስመጡ፣ ወይም በተደጋጋሚ የሰነድ ምርመራ፣ የፍተሻ እና የድህረ ዕቃ አወጣጥ ግኝት የሚገኝባቸው አስመጪዎች የሚያስመጧቸው ዕቃዎች፤ (ከTPRDP ወይም ከሌሎች በሲስተም ወይም በማኑዋል በተያዙ መረጃዎች መሠረት)
* ከጭነቱ ጋር የማይሄድ የተጋነነ ክብደት፣ ትራንስፖርት ወጪ፣ የኢንሹራንስ ክፍያ (ከዕቃው ጋር ተመጣጣኝ ያልሆኑ የትራንስፖርት ወይም የኢንሹራንስ ክፍያ መኖሩ ሲረጋገጥ)፤
* ተሽከርካሪው ከሚጠበቅበት ጊዜ በላይ ዘግይቶ ሲደርስና አሳማኝ ምክንያት ካልቀረበ፤
* መኪናው በተነሳበት ሁኔታ የደረሰ ካልሆነና አጠራጣሪ ሁኔታ ሲኖር (ሲሉ የተበጠሰ ከሆነ)
* የንግድ እቃዎች በብትን ጭነቶች ሲመጡ፤
* የሲል ቁጥር ልዩነት ሲኖር፤
* በክፍልፋይ የሚጓጓዙ የንግድ ዕቃዎች፤
* አዲስ አስመጪ ከሆነ (ይህም ሲባል በአጠቃላይ በተስተናገደቸው ቅ/ጽቤቶች ማስመጣት ከጀመረበት ቀን ጀምሮ ሦስትና ከሦስት ጊዜ በታች ሲያስመጣ አዲስ ሊባል ይችላል።
* እንዲሁም በየቀኑ ከሚመጡት በዝቅተኛ ከሚስተናገዱ ጭነቶች አልፎ አልፎ መረጣ /Random selection/ አምስት በመቶ (5%)፤

ለ) በዝቅተኛ (ነጭ) ስጋት ደረጃ የሚስተናገዱ፤

* ትላልቅ ወይም ግዙፍ ዕቃዎች ሆነው በዓይን በማየት ብቻ የሚለዩ ከሆነ (የፋብሪካና የፕሮጀክት ማሽነሪዎች እና ዕቃዎች)፣
* መንግስት ልዩ ትኩረት ሰጥቶ በልዩ ሁኔታ በቀረጥ ነፃ በCPC 421 የሚስተናገዱ ዕቃዎች፤
* በመንግስታዊና በመንግስት የልማት ድርጅቶች የሚገቡ ዕቃዎች፣
* በትምህርት ተቋማት የሚገቡ የትምህርት መገልገያ መሳሪያዎች፤
* በታማኝ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሾች (AEO) የሚገቡ ዕቃዎች፣
* በቪይና ኮንቬንሽን እና በሌሎች ስምምነቶች መሠረት ያለመፈተሽ መብት የተሰጣቸው ባለመብቶች እቃዎችን ሲያስመጡ፣

- በCPC 425 ተመላሽ ኢትዮጵያውያን ዲፕሎማቶች ይዘዋቸው የሚገቡ የግል መገልገያ ዕቃዎች እና የቤት ቁሳቁሶች፣
- በጉምሩክ ልዩ አገልግሎት ተጣቃሚ የሆኑ አምራች ድርጅቶች የሚገቡ ዕቃዎች፣
- ክፍት ጭነቶች ሆነው በማየት ብቻ ማለፍ የሚችሉ ከሆነ፤
- በመንገድ ወረቀቱ ላይ ጨረር አመንጪ ዕቃዎች የተገለጹ ከሆኑ (ነገር ግን ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ የተፈቀዱ ስለመሆናቸው ተገቢውን ማረጋገጫ ማድረግ እና የሚመጡት ዕቃዎች ጊዜ ያለፈባቸው አለመሆናቸውን ማረጋገጥ እንዲሁም አካላዊ ፍተሻ ማድረግ የሚቻሉ ዕቃዎች ከሆኑ አካላዊ ፍተሻ በማድረግ ማስተናገድ አስፈላጊ ነው)።
- ሌሎች በሙቀት፣ በቆይታ እና መሰል ምክንያቶች በቀላሉ ሊበላሹ የሚችሉ መድሃኒቶች ከላይ እንደተገለፀው እንዲሁም በስካኒንግ ማሽን የማይፈተሹ ዕቃዎች በዕቃ ፍተሻ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 119/2008 አንቀጽ 5 መሠረት ወይም በሌሎች የመሥሪያ ቤቱ የአሠራር ድንጋጌዎች፣ መመሪያዎች፣ ማኑዋሎች የማይፈተሹ ተብለው የተገለጹ ዕቃዎች ናቸው።

## 4.2. የወጪ ትራንዚት ቁጥጥር (የካርጎ ስካኖንግ ፍተሻ) ስጋት ደረጃ አጣጣል፣

### የተግባር መግለጫ

የወጪ ዕቃዎች ትራንዚት ቁጥጥርን በስጋት ስራ አመራር መሰረት ማከናወን፤

### አስፈላጊነት/Purpose

ሀገሪቱ ወደ ውጪ የምትልካቸው ምርቶች ጥራታቸውን ጠብቀው መውጣታቸውን እና ከተለያዩ ባዕድ ነገሮች ነፃ መሆናቸውን ለማረጋገጥ፤

### የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎች

- በትራንዚት ኢንስፔክተር የተረጋገጠ የመንገድ ወረቀት (T1)፤
- የትራንዚት ዲ/ዮን (EX8)፤
- የተደራጀ የስጋት መረጃ፤

## የአፈፃፀም ቅደም ተከተል/ Procedures

- ሰነድ ከትራንዚት ቁጥጥር ባለሙያ መቀበል፤
- ሲጋቶችን በመጣል ወደ ሚቀጥለው ስካኒንግ ዩኒት ማስተላለፍ፤

## ፈጻሚ አካል

- በቅ/ጽ/ቤቶች የሚገኙ የሲጋት ስራ አመራር ባለሙያዎች በተቀመጠላቸው የስራ መዘርዝር መሰረት የሚፈጽሙት ይሆናል።

በስካኒንግ ማሽን የማይፈተሹ ዕቃዎች በዕቃ ፍተሻ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 119/2008 ዓ.ም መሠረት ወይም በሌሎች የመሥሪያ ቤቱ የአሠራር ድንጋጌዎች፣ መመሪያዎች፣ ማኑዋሎች የማይፈተሹ ተብለው የተገለፁትን ጨምሮ በመነሻ ጣቢያ በዝርዝር ከተፈተሹ በመውጫ በር (የሲጋት አመላካች ያላቸውን ሳይጨምር) ከተገለጹት በስተቀር የኤክስፖርት ጭነቶች ሌሎች በብርቱካናማ ሲጋት ደረጃ ተመድበው በመውጫ በሮች የእየተረጋገጡ ይስተናገዳሉ።

- መነሻ ጣቢያ ላይ በዝርዝር የተፈተሸ ከሆነ መውጫ በር ላይ የማይፈተሽ ሲሆን፣ ነገር ግን አሳማኝ መረጃ ካለ ይፈተሻል
- መነሻ ጣቢያ ላይ በዝቅተኛ ሥጋት ደረጃ ካለፈ መውጫ ጣቢያ ላይ በአልፎ አልፎ መረጣ (Random Selection) አምስት በመቶ (5%) ፍተሻ ይከናወናል

# ምዕራፍ አምስት

## የገቢ መንገደኞች የስጋት ደረጃ አጣጣል፤

### የተግባር መግለጫ

ገቢ መንገደኞችን በስጋት ስራ አመራር መሰረት ማስተናገድ፤

### አስፈላጊነት/Purpose

የገቢ መንገደኞችን መስተንግዶ የተመጣጠነ ቁጥጥርና የተቀላጠፈ አገልግሎት እንዲኖር ለማድረግ፤

### የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎች

- የመንገደኞች ቅድመ-መረጃ (API- Advanced Passenger Information)፤
- የተደራጀ የሥጋት መረጃ (የመንገደኞች የኋላ ታሪክ)፤
- የስጋት ስራ አመራር መሠረታዊ ክህሎት፤

### የአፈፃፀም ቅደም ተከተል/ Procedures

- የመንገደኞች ቅድመ-መረጃ (API- Advanced Passenger Information) ከአየር መንገድ መቀበል፤
- መረጃውን መተንተን፤
- መንገደኛው ከመድረሱ በፊት ወይም መድረሱ ሲረጋገጥ ስጋቶችን ከዚህ በታች (ከሀ እስከ ለ) በተገለጸው መሰረት በመጣል ለቀጣይ ስራ ማስተላለፍ፤

### ፈጻሚ አካል

- በቅ/ጽ/ቤቶች የሚገኙ የስጋት ስራ አመራር ባለሙያዎች በተቀመጠላቸው የስራ መዘርዝር መሠረት የሚፈጽሙት ይሆናል።

ሀ) በዝቅተኛ (አረንጓዴ) ስጋት ደረጃ የሚስተናገዱ

- በመንገደኞች የስጋት ስራ አመራር መመሪያ መስረት በዝቅተኛ ስጋት ደረጃ ላይ ከሚመደቡ ሀገራት ለጉብኝት፤ ለዓለም አቀፍና አህጉር አቀፍ ስብሰባዎች ወይም ለኮንፈረስ የሚመጡ፤
- ለነፃ ህክምና አገልግሎት፤ ለሰብአዊ እርዳታ እና የትምህርት አገልግሎት ለመስጠት የሚመጡ፤
- ዲፕሎማቲክ መብት ያላቸው የኢትዮጵያ እና የሌሎች ሀገሮች መንገደኞች፤
- ለጥናትና ምርምር የሚመጡ መንገደኞች፤
- በመንግስታዊ እና በግል ተቋማት ለተለያዩ አገልግሎቶች ተጋብዘው የሚመጡ መንገደኞች፤
- ተመላሽ ኢትዮጵያውያን፤
- ለመጀመሪያ ጊዜ የሚመጡ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን፤
- የመንግስትና የግል ተቋማት ሰራተኞችና ኃላፊዎች ስልጠና፤ ኮንፈረንስ፤ ዎርክሾፖች ወይም ሴሚናሮች ተሳትፈው የሚመለሱ፤

ከላይ የተዘረዘሩት ዝቅተኛ (በነጭ) ለማስተናገድ እንደ መነሻ የተቀመጡት ሁኔታዎች ቢኖሩም ከአሁን ቀደም ተፈትሸው ልዩነት የሚገኝባቸው ድርጅቶች ከሆኑ፣ የስጋት አመላካቾች ካሉ ወይም በአልፎ አልፎ መረጣ (Randome Selaction) ከተመረጡ (ያለመፈተሽ መብት ያላቸውን ሳይጨምር) በከፍተኛ (በቀይ) የስጋት ደረጃ ሊስተናገዱ ይችላሉ።

ለ) በከፍተኛ (ቀይ) ስጋት ረጃ የሚስተናገዱ፤

- የጉዞው ዓላማ ለንግድ ከሆነ፤
- የማንኛውንም ድርጅት ዕቃ ይዘው የሚመጡ መንገደኞች (ከዲፕሎማቶች ውጪ)፤
- ተመላላሽ መንገደኛ (በሦስት ወር አንድ ጊዜና ከዛ በላይ) በተለያዩ ምክንያቶች ወደ ውጭ ሀገር ወይም በሀገር ውስጥ የሚመላለስ፤
- ከዚህ በፊት ሪከርድ የተያዘበት መንገደኛ፤
- የጉዞው መነሻ ሀገራት ከከፍተኛ ስጋት ደረጃ ያላቸው ሀገራት ሲሆን ( የሀገራት የስጋት ደረጃን ዳይሬክቶሬቱ በየሶስት ወሩ ከሚያሻሽለውና ከሚያስተላልፈው መረጃ ማግኘት ይቻላል)፤
- የተቆጣጣሪ መ/ቤቶች ፈቃድ የሚጠይቅ ዕቃ የያዘ መንገደኛ፤

- ለኤግዚቢሽን ጉዳይ ምርትና አገልግሎት ለማስተዋወቅ እና ለማዘጋጀት የሚመጡ፤
- በግል ጉዳይ ከሀገር ወጥተው የሚመለሱ፤
- ከፍተኛ የስጋት ደረጃ ካላቸው ሀገሮች ተላልፈው (through transit) የሚመጡ፤
- በዝቅተኛ ስጋት ደረጃ እንዲስተናገዱ የተዘረዘሩት ዲፕሎማቲክ መብት ካላቸው መንገደኞች ውጪ አምስት በመቶ (5%) በአልፎ አልፎ መረጣ (Randome Selaction)
- የመንገደኛው የትውልድ ሀገር በከፍተኛ ስጋት ደረጃ የሚመደብ ሲሆን
- የመንገደኛው የተለየና ያልተለመደ አካላዊ እንቅስቃሴ ሲያሳይ (ለምሳሌ መነጫነጭ፤ ያልተለመደ ላብ፤ ቅብጥብጥነት፤ ሚዛን ጠብቆ ያለመሄድ ወዘተ)
- ከሦስተኛ ወገን መረጃ ሲገኝ፤
- መንገደኞች ይዘውት የሚመጡት ጥቅል ከሚመጡበት ዓላማ አንጻር ብዛት ሲኖረው (ለምሳሌ ለትምህርት ወይም ለስብሰባ ሄዶ ሲመለስ ብዛት ያላቸው ሻንጣዎች ሲይዝ/ስትይዝ)፤
- በኢትዮጵያ በኩል ወደሌሎች ሀገሮች ትራንዚት የሚያደርጉ መንገደኞች ሆኖው በሀገር ውስጥ ቆይታ የሚያደርጉ ሲሆን፤
- መንገደኞች ይዘዋቸው በሚመጡ ዕቃዎች ላይ የጥርጣሬ ሪማርክ የተደረገበት፣ ከኢንተለጀንስ እና ከሌሎች አካላት የጥርጣሬ መረጃ የቀረበበት ሲሆን፤

ከላይ የተዘረዘሩት በከፍተኛ የሥጋት ደረጃ ለማስተናገድ እንደ መነሻ የተቀመጡት ቢኖሩም በተደጋጋሚ ተፈትሸው እንዲሁም ሠነዳቸው ተመርምሮ ልዩነት የማይገኝባቸውን ድርጅቶች በዝቅተኛ(በነጭ) የስጋት ደረጃ ሊስተናገዱ ይችላሉ።

# ምዕራፍ ስድስት

## የወጪ ዕቃዎች ስጋት አመዳደብ

**የተግባር መግለጫ**

**የወጪ ዕቃዎች ቁጥጥርን በስጋት ስራ አመራር መሠረት ማከናወን፤**

**አስፈላጊነት/Purpose**

በወጪ ዕቃዎች ላይ ሥጋትን መሠረት ያደረገ ቁጥጥርና የተቀላጠፈ አገልግሎት ተግባራዊ ለማድረግ፤

**የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎች**

- በፌዝቤት ተቀባይነት ያገኘ ሰነድ፤
- የተደራጀ መረጃ፤
- የሥጋት ሥራ አመራር መሠረታዊ ክህሎት፤

**የአፈፃፀም ቅደም ተከተል /Procedures**

- ሰነዶችን ከፌዝቤት መቀበል፤
- ስጋቶችን ከዚህ በታች በተገለጸው (ሀ እስከ ሐ) መሠረት መጣል፤

**ፈጻሚ አካል**

- በቅ/ጽ/ቤቶች የሚገኙ የስጋት ስራ አመራር ባለሙያዎች በተቀመጠላቸው የሥራ መዘርዝር መሠረት የሚፈጽሙት ይሆናል።

**ሀ)ዝቅተኛ የስጋት ደረጃ የሚመደቡ፤**

- ልዩ መብት ተጠቃሚ አምራች ድርጅቶች የሚልኳቸው ዕቃዎች፤
- ታማኝ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ ድርጅቶች /AEO/ የሚልኳቸው ዕቃዎች፤
- መንግስታዊ እና የመንግስት የልማት ድርጅቶች የሚልኳቸው ዕቃዎች፤

- አለማቀፍና አህጉር አቀፍ ድርጅቶች፣ ኤምባሲዎች እና ዲፕሎማቶች የሚልኳቸው ዕቃዎች (ለምሳሌ ተመላሾች)፤

ከላይ የተዘረዘሩት በአረንጓዴ ለማስተናገድ እንደ መነሻ የተቀመጡት ሁኔታዎች ቢኖሩም ከአሁን ቀደም ተፈትሸው ልዩነት የሚገኝባቸው ድርጅቶች ከሆኑ፣ የስጋት አመላካቾች ካሉ ወይም በእልፍ አልፎ መረጣ (Randome Selaction) ከተመረጡ (ያለመፈተሽ መብት ያላቸውን ሳይጨምር) በመካከለኛ ወይም በከፍተኛ የስጋት ደረጃ ሊስተናገዱ ይችላሉ፡፡

ለ) በመካከለኛ ስጋት ደረጃ የሚመደቡ፤

ከላይ በዝቅተኛ የስጋት ደረጃ የሚስተናገዱ ላኪዎች ከሚልኳቸው ዕቃዎች ውጪ

- የቁም እንስሳት፣
- ጫት፣ ቡና፣ አበባ፣ የቅባት እህሎች፣ ቅመማ ቅመሞች፣
- ቆዳ፣
- ሌሎች የተጓዳኝ መ/ቤቶች ፈቃድ የሚጠየቅባቸው ዕቃዎች፣

በተደጋጋሚ ሰነዳቸው ተመርምሮ ልዩነት የማይገኝባቸው ድርጅቶች ከላይ የተዘረዘሩት በቢጫ ለማስተናገድ እንደ መነሻ የተቀመጡ ሁኔታዎች ቢኖሩም በዝቅተኛ የስጋት ደረጃ ሊስተናገዱ ይችላሉ፡፡

በተደጋጋሚ ሰነዳቸው ተመርምሮ ልዩነት የሚገኝባቸው ድርጅቶች ከላይ የተዘረዘሩት በቢጫ ለማስተናገድ እንደ መነሻ የተቀመጡ ሁኔታዎች ቢኖሩም በከፍተኛ የስጋት ደረጃ ሊስተናገዱ ይችላሉ፡፡

ሐ) በከፍተኛ የስጋት ደረጃ የሚመደቡ፤

- ለጥገና ወደ ውጭ የሚላኩ ዕቃዎች፤
- በጊዜያዊነት ገብተው የነበሩት ዕቃዎች ሲመለሱ፤
- ታማኝ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ ድርጅቶች /AEO/ የሚልኳቸው ዕቃዎች በአልፎ አልፎ መረጣ (Randome Selaction) አምስት በመቶ (5%) እየታየ፤
- የልዩ የጉምሩክ አገልግሎት ተጠቃሚዎች የሚልኳቸው ዕቃዎች አልፎ አልፎ (Randome Selaction) አምስት በመቶ (5%) እየታየ፤

- በተለያዩ ምክንያቶች ወደ መጡበት ሀገር እንዲመለሱ የሚደረጉ ዕቃዎች፤
- ኤክስፖርት በሚያደርጉበት ጊዜ በተደጋጋሚ የፍተሻ ልዩነት በሚገኝባቸው ላኪዎች፤
- ከሶስተኛ ወገን መረጃ ሲገኝ፤
- ከሰነድ መርማሪ ወይም ከተለያዩ የስራ ክፍሎች ዕቃው እንዲፈተሽ ጥያቄ ሲቀርብ፤

ከላይ የተዘረዘሩት በከፍተኛ የሥጋት ደረጃ ለማስተናገድ እንደ መነሻ የተቀመጡት ቢኖሩም በተደጋጋሚ ተፈትሸው እንዲሁም ሠነዳቸው ተመርምሮ ልዩነት የማይገኝባቸውን ድርጅቶች በመካከለኛ ወይም በዝቅተኛ የስጋት ደረጃ ሊስተናገዱ ይችላሉ፡፡

<u>ማስታዎሻ፡-</u>

በወጪ ዕቃዎች ላይ የተጣለው የስጋት ደረጃ እንደተጠበቀ ሆኖ የሁሉም ወጪ ዕቃዎች ሰነድ እየተመረመረ ይስተናገዳሉ፡

## ምዕራፍ ሰባት

# ደረጃ አምስት፡ የስጋት ደረጃዎችን ውጤት መከታተል እና መገምገም

**የተግባር መግለጫ**

**የስጋት ደረጃዎች ከተጣሉ በኋላ ውጤታቸውን መከታተልና መገምገም፤**

አስፈላጊነት/Purpose

የስጋት ደረጃዎች ከተጣሉ በኋላ ውጤታቸውን መከታተልና በመገምገም በማኑዋል የተጣሉ ስጋቶችን መቀነስ፤ የሲስተም ክፍተቶችን በቀጣይነት ለማሻሻል እና የህግ ተገዥነት ደረጃ ለማሳደግ፤

**የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎች**

- የተደራጀ መረጃ፤
- የስጋት ስራ አመራር መሰረታዊ ክህሎት፤

**የአፈፃፀም ቅደም ተከተል/ Procedures**

- በሲስተምና በማኑዋል የተሰበሰቡ መረጃዎችን ማዘጋጀት፤
- ስጋቶችን ከዚህ በታች በተገለጸው መሰረት ውጤቱን መገምገምና ሪፖርት ማድረግ፤
    - ስጋት ከተጣለ በኋላ ውጤታማነቱን በመከታተል የስጋት ደረጃዎች ማሻሻያ ለማድረግ መረጃዎች በመተንተን ለማዕከል ሪፖርት በሲስተም/TPRDP/ እና በማኑዋል ማድረግ፤
    - የህግ ተገዥነት ችግር ያለባቸው ደንበኞች በቅ/ጽ/ቤት ደረጃ በመለየት አስፈላጊው ድጋፍና ሥልጠና መስጠት፤ በልዩ ሁኔታ ከፍተኛ ጥፋት ያለባቸው ደግሞ በወቅቱ በመለየት ለሚመለከተው አካል (የሥራ ክፍል) ሪፖርት ማድረግ፤
    - በሥጋት ስራ አመራር እመካኝነት የተጣሉ ስጋት ደረጃዎች አፈጻጸማቸውን በመከታተልና በመገምገም ውጤታማነታቸው ማረጋገጥ፤
    - የቁጥጥር እና የተሳለጠ አገልግሎት አሰጣጥ የተመጣጠነና ውጤታማ መሆኑ በየወቅቱ በመገምገም እንዲሻሻል ማድረግ፤

- የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አፈጻጸም ውጤት (የፍተሻ፣ ሰነድ ምርመራ፣ ትራንዚትና መጋዘን ቁጥጥሮች) እንዲሁም የድህረ-ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ውጤት በተመለከተ የሚያዙ መረጃዎች በተፈለገው ጥራት ደረጃ መያዛቸውን መከታተል ፤
- የመረጃ ቋት ሲስተም ውጤታማ እንዲሆን ክትትል ማድረግ፣ ሥልጠና መስጠት እና የማሻሻያ ጥናት ማድረግ፤

**ፈጻሚ አካል**

- በቅ/ጽ/ቤቶች የሚገኙ የሥጋት ሥራ አመራር ባለሙያዎች በተቀመጠላቸው የሥራ መዘርዝር መሠረት የሚፈጽሙት ይሆናል፡፡

<u>ማስታወሻ፦</u>

- የሥራ ኃላፊነትን በተመለከተ በሥራ መዘርዝር ላይ በተቀመጠው የኃላፊነት ደረጃ መሠረት በየደረጃው ባሉ ባለሙያዎች የሚወሰን ሲሆን፤ የተለየ ሁኔታ ሲያጋጥም የቅ/ጽ/ቤቱ አመራር ውሳኔ የሚሰጥበት ይሆናል፡፡
- በአፈጻጸም ወቅት የሚያጋጥሙ ችግሮች ሲኖሩ እንደ አስፈላጊነቱ በሥጋት ሥራ አመራር ዳይሬክቶሬት በኩል በማኑዋሉ ላይ ማሻሻያ ይደረጋል፡፡
- ይህ ማኑዋል እንዳስፈላጊነቱ ታይቶ ተቋሙ ሲያምንበት ሊሻሻል ይችላል፡፡